# አዲስ ዘመን

እፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 108 ታኅሣሥ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በተሰራው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ ኢትዮጵያ ወደ መደበኛ አለም አቀፍ ግንኙነት ተመልሳለች


ሞገስ ጸጋዬ


አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሁለት አመታት የገጠሙ የውስጥና የውጭ ችግሮችን ለመፍታት በተሰራው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ ኢትዮጵያ ወደ መደበኛ አለም አቀፍ ግንኙነት መመለሷን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የአምባሳደሮች ዓመታዊ ስብሰባና ስልጠና ከትናንትናው ዕለት ጀምሮ ሱሉልታ በሚገኘው የአፍሪካ አመራር ልህቀት ማዕከል መሰጠት ተጀምሯል።

በዓመታዊው የአምባሳደሮች ስብሰባ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፣ ባለፉት ሁለት አመታት በተሰራው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ አገራችን ወደ መደበኛ አለም አቀፍ ግንኙነት ተመልሳለች። ስብራታችንን የመጠገንና መልሶ ወደ ነበረውና ወደ ተሻለው ግንኙነት ለመሸጋገር ዕድሎች ተፈጥረዋል። ኢትዮጵያን ገጥመዋት የነበሩ ፈተናዎችን የተሻገርንበት ስልት ታሪካዊና የምንኮራበት ነው። በሁሉም ዘርፍ ችግሮችን ለመሻገር አምባሳደሮች ያደረጉት ዘመቻ የሚያኮራና የሚመሰገን ነው። ወደፊትም አሁን ካለው ጥረት በላይ ጠንክሮ በመስራት የኢትዮጵያን ተቀባይነት ማሳደግና ብሔራዊ ጥቅሟን የማስጠበቅ ስራ መሰራት እንዳለበት ተናግረዋል።

አምባሳደሮች የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመጥንና ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስከብር እንቅስቃሴ አድርገዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የትኛውንም ድል እያስመዘገብን ብንጓዝ በአለም አቀፍ ግንኙነት ረገድ አጀንዳ የሆኑ ጉዳዮችን እየፈቱ መሄድ ያስፈልጋል። ሁሌም አዲስ አጀንዳ


በተሰራው ጠንካራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ደመቀ መኮንን













## “የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ማቅናት የሰላም ሂደቱን ስኬታማነት እና የመንግሥትን ቁርጠኝነት ያሳያል”

- ኡስታዝ ከሚል ሸምሱ


ዋቅሹም ፍቃዱ


አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ መቀሌ ማቅናት የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት አበረታች ደረጃ ላይ መሆኑንና መንግስት ለሰላም ቁርጠኛ አቋም መያዙን ያመላክታል ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ ገለጹ፡፡


“የልዑካን ቡድኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር

## በሦስት ወራት 472 ሺህ ቶን ጭነቶችን አጓጓዘ

- ከ 36 ሺህ በላይ መንገደኞችም ተጓጉዘዋል


ዳግማዊት ግርማ


አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሦስት ወራት 472 ሺህ ቶን ጭነቶችንና 36 ሺህ መንገደኞችን ማጓጓዙን ኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት ስታንዳርድ ጌጅ ባቡር አክሲዮን ማህበር አስታወቀ፡፡ የባቡር አገልግሎቱ የሁለቱ ሀገራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ አወንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሚገኝም ተመላክቷል፡፡

የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር አብዲ ዘነበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድርጅታቸው በሦስት ወራት ውስጥ ብቻ 472 ሺህ ቶን ጭነቶችንና 36 ሺህ መንገደኞችን ማጓጓዝ ችሏል፡፡

እንደ ዶክተር አብዲ ገለፃ፤ ኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በጭነት ማመላለሻ ባቡሮች 348 ጊዜ ባደረጉት ምልልስ ክብደታቸው 472 ሺህ ቶን የሚመዝኑ የተለያዩ ጭነቶችን በማጓጓዝ አገልግሎት መስጠት ችሏል፡፡


የኢትዮ-ጅቡቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ዶክተር አብዲ ዘነበ

# አክሱም

## እንደምን ሰነበተች? እንደምንስ አለች?


አዲሱ ገረመው


በኢትዮጵያ ታሪክ ልዩ ሥፍራ ከያዙት ቦታዎች የአክሱም ከተማ አንዷ ናት፡፡ አክሱም የኢትዮጵያ የታሪክና የሃይማኖት ከተማ ስትሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደተቆረቆረች መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ አክሱም የቤተ ክህነቱም ሆነ የቤተ መንግሥቱ ማዕከል በመሆን ለብዙ ዘመናት አገልግላለች፡፡ በተለይም የታቦተ ጽዮን መንበር በመሆኗ ከተማዋ ድንቅ አድናቆትን ተጎናጽፋለች፡፡


አክሱም እንደምን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









“የዳበረ ዕውቀት ለማግኘት ጠንካራ የንባብ ባህል ሊጎለብት ይገባል”

- አቶ ግሩም ተማም

የሚዛን አማን ከተማ ከንቲባ


ገጽ 3

# የአደረጃጀት ጥያቄዎች የሀገርን ዘላቂ ጥቅም በሚያረጋግጥ መንገድ ምላሽ እያገኙ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- የአደረጃጀት ጥያቄዎች የህዝብን እና የሀገርን ዘላቂ ጥቅም በሚያረጋግጥ መንገድ ምላሽ እያገኙ ነው ሲሉ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እርስቱ ይርዳው ገለጹ፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምስረታና ነባሩን በአዲስ የማደራጀት ማስፈፀሚያ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት የክልሉ አብይ ኮሚቴ በተገኘበት የአፈፃፀም ሪፖርቱን በዲላ ከተማ ትናንት ሲገመግም የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እርስቱ ይርዳው እንደገለፁት፤ የክልሉ ህዝብ ለበርካታ ዘመናት ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ ጥያቄ ሲያነሳ ቆይቷል።

ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች የመልካም አስተዳደር ችግር ከመሆንም አልፎ የግጭት መንስኤ ሲሆን ቆይቷልም ነው ያሉት፡፡

የአደረጃጀት ጥያቄው በተናጠል የተያዙ ሀሳቦችን በማቅረብ የበለጠ ተጠቃሚ በሚያደርግ መንገድ መቃኘቱ እና ዘላቂ ጥቅም በሚያስገኝ አኳያ ከስምምነት መደረሱን አቶ እርስቱ ጠቅሰዋል።

ስምምነቱም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ መሰጠቱንም ርዕሰ መስተዳድሩ ገልጸዋል።

በክልሉ አሁን ያሉ ህዝቦች ሁለት ክልል ሆነው እራሳቸውን ችለው የሚያደራጁበት ሁኔታ እንዲፈጠር የመነሻ ውሳኔ መሰጠቱንም ተናግረዋል፡፡

የአንዱ ክልል ህዝበ ውሳኔ እየተካሄደ መሆኑን የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ቀሪው የህዝቦችን ጥያቄ ምላሽ መስጠት በሚያስችል መንድ እራሱን መልሶ እንዲያደራጅ አቅጣጫ መቀመጡንም ነው የጠቆሙት፡፡

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት የህዝበ ውሳኔውንና ህዝበ ውሳኔውን ተከትሎ ለሚመጣው ውጤት የአደረጃጀት ስራው በደንብ እንዲመራ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት መቋቋሙንም አስረድተዋል።



አቶ እርስቱ ይርዳው

ህዝበ ውሳኔውን ተከትሎ ለሚመጡ ውሳኔዎች ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ከክልሉ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።



ዶክተር አያሌው ወንዴ

## 1900 ሄክታሩ የጣና ሐይቅ በእምቦጭ አረም ተወሯል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከጣና ሀይቅ 1900 ሄክታሩ በእምቦጭ አረም መወረሩን የጣና ሐይቅና ሌሎች ውሃማ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡

የጣና ሐይቅና ሌሎች ውሃማ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር አያሌው ወንዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጣና ሐይቅ ላይ ከተከሰተ 12 ዓመታትን ያስቆጠረው የእምቦጭ አረም በአሁኑ ወቅት የሐይቁን 1900 ሄክታር ሸፍኗል፡፡

የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች አረሙን በጨረር እና በባህላዊ ዘዴ ለማጥፋት የሚያስችል ግኝት አለን በሚል አረሙን ለማጥፋት ሙከራ ቢያደርጉም እስካሁን አመርቂ ውጤት እንዳልመጣ ጠቁመዋል፡፡

የአረሙ የመዛመት መጠን በፊት ከነበረው መጠን መቀነስ ቢያሳይም አሁንም የእምቦጭ አረም የጣና ስጋት ሆኖ መቀጠሉንም ዶክተር አያሌው ገልጸዋል፡፡

የእምቦጭ አረምን የማጥፋት ዘመቻ የህብረተሰብ ተሳትፎ ቢያስፈልገውም ክልሉ የነበረበት የሰላም እጦት ስራቸው ላይ ተግዳሮት ፈጥሮ መክረሙን የገለጹት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ አሁን ላይ ግን በአካባቢው የተሰሩ የሰላም ስራዎች ውጤት እያሳዩ በመሆናቸቸው አረሙን ወደ ማጥፋቱ ስራ በሙሉ ልብ ለመግባት እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ነው የተናገሩት፡፡

እንደ ዋና ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በ2015 በጀት ዓመት ኤጀንሲያቸው የእምቦጭ አረሙን የማጥፋት እቅድን ይዞ በመስራት ላይ ያለ ሲሆን፤ እቅዱም በሰው ሃይልና በማሽን ታግዞ የመስራት ስራዎች ተጀምረዋል፡፡

ዋና ስራ አስኪያጁ እንዳስታወቁት፤ የእምቦጭ አረም በሐይቁ አካባቢ ከ30 በላይ ቀበሌዎችን ማዳረስ የቻለ ሲሆን፤ በአንዳንዶቹ ስፍራዎች ከአስር እስከ ስድስት መቶ ሄክታር ሽፋን ያለው ሲሆን፤ እንደየብዛትና ጥልቀቱም ከሰው ሃይል እስከ ማሽን በመጠቀም የማጥፋት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል፡፡

የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች አረሙን በጨረር የማጥፋት፣ በባህላዊ ዘዴ ለማጥፋት የተለያየ ግኝት አለን የሚሉ አካላት ጥረቶች ቢያደርጉም ያለመሳካቱንም ዋና ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡

የተለያዩ ባለሀብቶችና የመንግሥት ተቋማት ሐይቁ ላይ ለሚገኘው አረም የማጥፊያ ስራው የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ቃል የገቡ ቢሆንም ቃላቸውን እንዳልፈፀሙ የገለጹት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ የእምቦጭ አረምን ለማስወገድ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪያቸውንም አቅርበዋል፡፡

የፌደራል መንግስት ከክልሉ በመሆን የእምቦጭ አረምን ለማጥፋት የሚሆኑ ስራዎችን ለመከወን የጋራ እቅድ የታቀደ ሲሆን ለተግባራዊነቱም የመንግሥትን ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙም ዋና ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡



## ባለፉት አምስት ወራት 663 አዳዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ስራ ገብተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ብቻ 663 አዳዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ስራ መግባታቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገለፁ።

ኢንዱስትሪዎቹ 130 የሚሆኑት መካከለኛ፣ 5ቱ በጣም ከፍተኛ ቀሪዎቹ በአነስተኛ ደረጃ ያሉ ሲሆኑ፤ እስከ 9,600 የሚደርስ የስራ ዕድል የፈጠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ የገቢ ምርትን ለመተካት ትኩረት ሰጥቶ ባከናወነው ስራ 708 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ አምርቶ መተካት ተችሏል ብለዋል።

“አሁን በተከተልነው አቅጣጫ ከውጭ ስናመጣቸው የነበሩ አንዳንድ ምርቶችን ከራሳችን አልፎ ለወጪ ንግድ ማቅረብ ችለናል” ብለዋል ሚኒስትሩ።

ባለፉት አምስት ወራት 161 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያወጡ ምርቶች ወደ ውጭ የተላኩ ሲሆን፤ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብልጫ የታየበት መሆኑን ገልፀዋል።

በአጠቃላይ ዘርፉ መነቃቃት የጀመረበት፣ የአመራር ትኩረት ያገኘበት፣ ባለሃብቶችም በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ወደ አዳዲስ ኢንቨስትመንት መግባት የጀመሩበት ወቅት እንደሆነ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል መናገራቸውን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ቤተ-መጽሐፍቱ ከ20 ሺህ በላይ ተገልጋዮችን የሚያስጠቅም ዋይፋይ ሊዘረጋ ነው

**አማን ረሽድ**

አዲስ አበባ፡- በአንድ ጊዜ ከ20 ሺህ በላይ ተገልጋዮችን ሊያስጠቅም የሚችል ዋይፋይ ለመዘርጋት እየተሰራ መሆኑን የአብረሆት ቤተ-መጽሐፍት አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የአብረሆት ቤተ-መጽሐፍት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ውባየሁ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በቤተ-መጽሐፍቱ በአንድ ጊዜ ብቻ ከ20 ሺህ በላይ ተገልጋዮችን ሊያስጠቅም የሚችል ዋይፋይ ሊዘርጋ ነው፡፡

ከዋይፋይ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከቤተ-መፅሐፍቱ ተገልጋዮች የሚነሱ ቅሬታዎች እንዳሉ የገለጹት ኢንጂነር ውባየሁ ፣ በቤተ-መጽሐፍቱ ችግሩ መኖሩን አመላክተዋል፡፡

ይህንንና መሰል ችግሮችን በመሠረታዊነት ለመፍታት ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በጋራ በመሆን የዋይፋይ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የዋይፋይ መሰረት ልማት ማስፋፊያ እና ዝርጋታ ስራው እስኪያልቅ ድረስ ተገልጋዮች በትዕግስት እንዲጠባበቁም ኢንጅነሩ አሳስበዋል።

አብረሆት ቤተ-መጽሐፍት አገልግሎት መስጠት ከጀመረ አንድ ዓመት ከሁለት ወር እንደሞላው ያወሱት ኢንጅነሩ፣ ቤተ-መጽሐፍቱ በቀን ከ43 ሺ በላይ ተጠቃሚዎችን የማስተናገድ አቅም ያለውና አሁን ላይ በቀን ከ 7000 በላይ ተጠቃሚዎችን እያገለገለ ነው ብለዋል፡፡

ቤተ-መጽሐፍቱ ከማንበቢያነት ባሻገር በውስጡ የአንፊ ቲያትር፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የልጆች መዋያና እናቶች ልጆቻቸውን የሚመግቡበት ክፍልን በውስጡ ያካተተ ቤተ መጽሐፍት እንደሆነም አመላክተዋል።

አብረሆት ቤተ-መጽሐፍት ኢንተርናሽናል ቤተ-መጽሐፍቶች ሊያሟላቸው ከሚገቡ ነገሮች ውስጥ የአባልነት ፕሮግራም ነው ያሉት ኢንጅነሩ፣ የአባልነት ፕሮግራም የተጀመረበት በሁለት ምክንያቶች ነው ያሉ ሲሆን አንዱና ዋነኛው ማህበረሰቡ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት እንዲገለገልበትና በሌላ በኩል ማህበረሰቡ የማንበብ ባህሉን እንዲያጎለብት የሚያደርግ ነው ብለዋል።

የቤተ-መጽሐፍቱ አባል መሆን ሲቻል የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖራሉ ያሉት ኢንጅነር ውባየሁ፣ ከጥቅሞቹ ውስጥ አንዱ ማንኛውንም መፅሐፍት ቤቱ ወስዶ ማንበብ ያስችላል ብለዋል።

በሌላ በኩልም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ1.3 ሚሊዮን በላይ የተለያዩ ጋዜጦችን እና የህትመት ውጤቶችን ለግሷል፣ እነኝህን ቤተ-መጽሐፍት አባሎቹ በኦንላይን በየትኛውም ቦታ እንዲጠቀም ያስችላል ብለዋል።

ለ10 ሴቶችና ለሁለት ወንዶች የውጭ የትምህርት ዕድልን ለአባላቱ የሚሰጥ ፕሮግራም ቤተ-መጽሐፍቱ እንዳለውም ጠቁመዋል፡፡

ቤተ-መጽሐፍቱ ሰፊ ስለሆነ ከአራት ሚሊየን በላይ መጽሐፍት ያስፈልጉታል፣ መጽሐፍቱን ክልሎችንና ህብረተሰቡን በማሳተፍ በመሰብሰብ ላይ እንደሚገኝ የጠቀሱት ኢንጅነሩ፣ ይህ በቂ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቤተ-መጽሐፍቱ የድንገተኛ ጊዜ ጥሪ ማሳወቂያ የተገጠመለት ነው፡፡ በመሆኑም የቤተ-መፅሐፍቱ ተገልጋዮች የአጠቃቀም ህጎችን ሲጥሱ የተገጠመለት የሴንሰር ማሽን የድንገተኛ ጊዜ ጥሪ እንደሚያሰማና በዚህ ምክንያት ተገልጋዮች ይረበሻሉ፡፡ ተገልጋዮቹ የተቀመጡ ህጎችን በማክበር መገልገል እንደሚገባቸው ኢንጂነሩ ገልፀዋል።

ማህበረሰቡ ቤተ-መጽሐፍቱ የህዝብ መሆኑን በመረዳት የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት እንዲገለገልና የአባልነት ምዝገባ ፕሮግራም እድሉን እንዲጠቀሙበት ኢንጂነሩ ለተጠቃሚዎች ሁሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



# በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የህፃናት ማቆያ ውስጥ የሚውሉ ህፃናት የኩፍኝ ክትባት ወሰዱ

**አስመረት ብስራት**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የህፃናት ማቆያ ውስጥ የሚውሉ ህፃናት የኩፍኝ ክትባት ወስደዋል።

የተቀናጀ የኩፍኝ ክትባት ዘመቻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለተከታታይ አስር ቀናት የሚሰጠው የክትባት ዘመቻው ከታኅሣስ 13 ጀምሮ እየተሰጠ ሲሆን እስከ ታህሳስ 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሚቀጥል ነው፡፡

የኩፍኝ ክትባት ከዘጠኝ ወራት በላይ እድሜ ላላቸው ህፃናት የተሰጠ ሲሆን በዕለቱ የምግብ እጥረት ያለባቸውን ህፃናት ልየታና የምክር አገልግሎት፤ የሆድ ጥገኛ ትላትሎች መድሃኒትና ቫይታሚን ኤ ለአስራ ሁለቱም ህፃናት መሰጠቱን ከባሻ ወልዴ ችሎት ጤና ጣቢያ የመጡት የጤና መኮንን ቃልኪዳን ያረጋል ተናግረዋል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ ቀጣና ላሉት ነዋሪዎች ቤት ለቤትም ሆነ በጤና ጣቢያዎች ውስጥ ክትባት እየሰጡ መቆየታቸውን ተናግረው፤ ህብረተሰቡ በፍፁም ቀናኢነት እያደረገ ስላለው ትብብር ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ክትባት ሲያስከትቡ ያገኘናቸው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሰራተኛ ወይዘሮ ስምረት ያዛቸው እንደተናገሩት፤ የአንድ አመት ከአንድ ወር የሆነው ህፃን ልጃቸውን ሳይንገላቱ በመስሪያ ቤታቸው ቅጥር ግቢ መሰጠቱ እንዳስደሰታቸው ገልፀዋል።

ሌላዋ እናት ወይዘሮ ሀገርነሽ ወርቁ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ሴት ሰራተኞች ከስራ ገበታቸው ሳይስተጓጎሉ ህፃናት ልጆቻቸውን በቅርበት በማግኘት በእረፍት ሰዓታቸው ልጆቻቸውን እያጠቡ እንክብካቤ ማድረጋቸው ትልቅ እድል መሆኑን ገልፀው፤ ይህንን ምቹ የስራ ሁኔታ ለፈጠሩት የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ክትባቱንም በተቋሙ ቅጥር ግቢ የህክምና ባለሙያዎች መጥተው መስጠታቸው ስራቸው እንዳይበደል እንዲሁም ድካምና እንግልት እንዳይኖር ማድረጉ እንዳስደሰታቸውም ተናግረዋል።

የተቋሙ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጉዳይ ተጠባባቂ ኃላፊ ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ እንደተናገሩት፤ ከተቋሙ አቅራቢያ ከሚገኘው ባሻ ወልዴ ጤና ጣቢያ ጋር በመተባበር በተቋሙ የሚውሉ ህፃናት ጤናን የመከታተል ስራ የሚከናወን መሆኑን ተናግረዋል።

አሁንም በህፃናት ማቆያው የሚውሉ ህፃናትን ክትባት ያሉበት ቦታ ድረስ በመምጣት የህክምና ባለሙያዎቹ ክትባቱን በመስጠታቸው አመስግነዋል። እናቶች ከልጆቻቸው ሳይለዩም ስራቸውንም ሳያቋርጡ የተለያዩ የህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውም የሚደገፍ ተግባር መሆኑን አብራርተዋል።

# “የዳበረ ዕውቀት ለማግኘት ጠንካራ የንባብ ባህል ሊጎለብት ይገባል”

-አቶ ግሩም ተማም
የሚዛን አማን ከተማ ከንቲባ

**ሳሙኤል ወንደሰን**




ሚዛን አማን፡- በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ የዳበረ ዕውቀት ለማግኘት ጠንካራ የንባብ ባህል ሊጎለብት ይገባል ሲሉ የሚዛን አማን ከተማ ከንቲባ አቶ ግሩም ተማም ተናገሩ።

“መጻህፍት ለዕውቀት ገበታ፤ መዛግብትና የጽሑፍ ቅርሶች ለዘመን ትውስታ!”በሚል መሪ ሃሳብ የንባብ ሳምንት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን አማን ከተማ ተካሂዷል።

በወቅቱ ከንቲባ አቶ ግሩም ተማም፤ ክልሉ በንባብ ባህል የዳበረ ብቁ ተማሪዎች እና የዳበረ እውቀት ያለው ነዋሪ እንዲፈጠር ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ጠንካራ የንባብ ባህል አስፈላጊ ነው። የንባብ ሳምንቱ በክልሉ ብቁና ተወዳዳሪ ተማሪዎችን ለማፍለቅ እንዲሁም የከተማዋ ነዋሪዎች የዳበረ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ሁነቱ ለትውልድ የንባብ ባህል በማካፈልና አንባቢ ትውልድ በመፍጠር እንዲሁም ለአገሩ የሚጠቅም ዜጋ ለማፍራት እንደሚረዳ የተናገሩት አቶ ግሩም፤ ወጣቶች ጊዜያቸውን በማንበብ ቢያሳልፉ ውጤታማነታቸው ላይ በጎ ሚና ይጫወታል ሲሉ አስረድተዋል።

ንባብ ለዘመናት የምንሰራቸውን ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ማወቅ የምንችልበት መንገድ ነው።ከዚህ ባለፈ ከንባብ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች መፍጠር ይቻላል። በአጠቃላይ ሲታይም የንባብ ውጤቱ ሰዎች ኑሯቸውን በቀላሉ እንዲመሩ የሚረዳ በመሆኑ ትውልዱ የንባብ ባህሉን ሊያዳብር ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ ግሩም ገለፃ፤ የንባብ ባህሉን ለማዳበር በአብዛኛው አካባቢዎች ምቹ ሁኔታ የለም። በሚዛን አማን ከተማ ከትምህርት ቤቶች ውጪ ያሉት ቤተ መጻሕፍት ሁለት ብቻ ናቸው። ይህም በከተማው የዳበረና ችግር ፈቺ ትውልድ ለመፍጠር በቂ አይደለም።

ስለዚህ የንባብ ባህሉን ሊያዳብሩ የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል። በከተማዋ የተዘጋጀው የንባብ ሳምንትም በርካታ ቤተ መጻሕፍት ለመገንባትና የማንበብ ፍላጎት ያለው ትውልድ ለመፍጠር እንደማነቃቂያ ያገለግላል ብለዋል።

በንባብ ሳምንቱ ምክንያት በርካታ መጻሕፍት ወደከተማዋ በመግባታቸው ነዋሪዎች እንዲጠቀሙባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

የንባብ ሳምንቱን የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጽሃፍት አገልግሎት ከሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ፣ የቤንች ሸኮ ዞን ባህል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ እንዲሁም የሚዛን-አማን ከተማ አስተዳደር በጋራ አዘጋጅተውታል።

የንባብ ሳምንቱም ከታህሳስ 15 እስከ ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የተካሄደ ሲሆን፤ በዝግጅቱ ላይ መጽሐፍ አታሚዎችና አሳታሚዎች፣ ደራሲያን፣ የመጻህፍት አከፋፋዮችና በንባብ ላይ የሚሰሩ የመንግስትና የግል ተቋማት ተሳትፈዋል።

# አክሱም እንደምን ሰነበተች? ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዘመናችንም ከአገር ውስጥ እስከ ውጪ ባሉ ዜጎች የምትጎበኝ ታላቅ ከተማ መሆኗ ይነገርላታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ኅዳር 21 ቀንን በታላቅ ክብር ስታከብር በዚሁ ዕለት ምእመናን በዓሉን ለማክበርና ለመሳለም ወደ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በብዛት ይገሠግሳሉ፤ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ መባውን ይሰጣሉ።

አክሱም ይህን ጸጋ ብትጎናጸፍም በሰሜኑ ግጭት ምክንያት ድምጿ ጠፍቶ፤ ሠላም ርቋት፣ ህዝብ ናፍቋት መቆየቷን የአካባቢው የሃይማኖት አባቶች ለኢፕድ ይናገራሉ። ቄስ በሪሁ ገብረእግዚአብሔር ይባላሉ የርዕሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን አገልጋይ ናቸው። ባለፉት ሁለት ዓመታት በነበረው ጦርነት ምክንያት ለወትሮ በቱሪስት ትጥለቀለቅ የነበረችው ከተማ ምድረ በዳ እስክትሆን ድረስ ጭር ብላ መቆየቷን ይናገራሉ። "በሰላም እጦት ሕዝቡ ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላው ተንቀሳቅሶ ሰርቶ ለመብላት ይቸገር ነበር። ጊዜው የጭንቅና የረሃብ ሆኖ ቆይቷል። ተማሪዎች ቤት እንዲውሉ ተደርገዋል። ህክምና እንደ ልብ ማግኘት ያስቸግር ነበር" ይላሉ የጦርነቱን ወቅት ሁኔታ እያስታወሱ።

ከጦርነቱ በፊት፤ የአካባቢው ሰው ሌት ከቀን ሰርቶ ኑሮውን በአግባቡ ይመራ እንደነበር የሚያስታውሱት ቄስ በሪሁ፤ የሁለት ዓመቱ ጦርነት ጊዜ ግን ለምኖ ማግኘት እንኳን የማይቻለበት መጥፎ ወቅት እንደነበር ይገልጻሉ። የጦርነቱ ዳፋ ባለ ሀብቱንም ድሃውንም እኩል ያሰቃየ በሰው ልጅ ህይወት መከሰት ያልነበረበት እንደሆነም ነው የሚጠቅሱት።

"ጥሬ ቢገኝ አስፈጭቶ ለመብላት አማራጭ አልነበረም። ምክንያቱም መብራት የለም። ይህ ደግሞ ቀኑን ጨለማ አድርጎብን ቆይቷል" ይላሉ ቄስ በሪሁ።

ሠላምን እንደ ነፍሱ የሚውደው ህዝብ ሠላም ሲናፍቅ እንደነበር። በሠላም ስምምነቱ ዛሬ ላይ እፎይታን አግኝቷል በማለት፤ አሁን ላይ የመሠረታዊ አገልግሎቶች እየተመለሱ እንደሆነና በተለይ የመብራት አገልግሎት ከተጀመረ ወዲህ እህል አስፈጭቶ መብላት እንደተቻለ፤ በስልክ ከወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር መገናኘት እንደቻሉ በመግለጽ፤ ሕዝቡ ዘላቂ ሠላም እንዲመጣ ትልቅ ፍላጎት እንዳለው ነው የተናገሩት።

ኢትዮጵያ እንደ ሃገር አንድ ሆና፣ ሕዝቦቿ በዘር በቋንቋና በሌላም ሳይለያዩ በሠላም እንዲኖሩ፣ ተዛምዶና ተዋልዶ ያለው ማህበረሰብ ተቀራርቦ እንዲኖር አባታዊ ምክራቸውን ሰጥተዋል።

ቄስ በሪሁ፤ "በሠላም እንጂ በጦርነት የሚፈታ ነገር እንደሌለ አይተናል። የሠላም እጦት አገርን ወደ ኋላ የሚጎትት እንጂ የሚያሳድግ አይደለም። ጦርነት ሰውን የሚበላ ሃገርን የሚያወድም ነው። በጦርነት የሚመጣ የአገር ዕድገት የለም። በቀጣይ ከግለሰብ ጀምሮ ሁሉም አካል ኃላፊነቱን ተወጥቶ ዘላቂ ሠላም መስፈን አለበት። ህዝብን ሰቆቃ ውስጥ የሚከት የጥይት ኮሽታ ዳግም እንዲሰማ አንፈልግም" ሲሉም መክረዋል።

ወጥቶ መግባትና በልቶ ማደር የሕዝቡ ትልቁ ችግር እንደነበር የሚያስታወሱት ደግሞ አባ ገብረመድኅን ገብረኪዳን ናቸው። ይህ ለአክሱም የማይገባ ነበር በማለት፤ ትልቅ ታሪክ ያላት ስፍራ በጨለማ ውስጥ መክረሟ ሁሉንም ያሳዘነ እንደሆነ ገልጸዋል። በዓለም የቱሪስት መዳረሻ ሆና የውጭ ዜጎች የሚጉርፉባት ከተማ ዝር የሚልባት ሰው አጥታ፤ ጦርነቱ መጥፎ ጥላ አሳርፎባት ማለፏን አስታውሰዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የቤተ ክርስቲያን ቅዳሴና ሰዓታት ያልተቋረጠባት አክሱም ጽዮን ሌትና ቀን ስለ ሠላም ፈጣሪዋን ስትለምን ከርማለች። ይሁንና ዛሬ ላይ የፈነጠቀው ሠላም ምዕመኖቿን ደስታ አጎናጽፏል። መላው የአካባቢው ሕዝብም ከጨለማ ወጥቷል። ያለ ሰቀቀን ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳል። የጸጥታ አካላት በስፍራው በመኖራቸውም ያለ ስጋት ማኅበራዊ እንቅስቃሴያችንን እናደርጋለን።

የሠላም ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሆኖ ሰው የናፈቃት ከተማ ዳግም ሰው እየጎረፈባትና፣ ሽር ጉድ ብላ እንግዶቿን ተቀብላ የምትታይበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አባቶቹ ተመኝተዋል።



ቄስ በሪሁን ገብረእግዚአብሔር



አባ ገብረመድኅን ገብረኪዳን

## የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይህም እንደ ሃገር ማጓጓዝ ከተቻለው የወጪ ገቢ ጭነት መጠን 15 በመቶውን ይሸፍናል፡፡

ኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት ከጭነቶች በተጨማሪ መንገኞችንም የሚያስተናግድ ሲሆን በመስመር ላይ የመንገደኛ ማመላለሻ ባቡሮች 109 ጊዜ ባደረጉት ምልልስ 36 ሺህ መንገደኞችን ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች ማጓጓዝ መቻሉን ዶክተር አብዲ ተናግረዋል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቡና ምርት ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ስታገኝ 98 ከመቶ ያህሉ ቡና የተጓጓዘው በባቡር እንደሆነ ያወሱት ዶክተር አብዲ፤ ጭነቶችን በማጓጓዝ ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ እየሆነ መምጣቱን ነው የተናገሩት፡፡

ድርጅቱ በፈረንጆቹ የጊዜ ቀመር 2021 ያገኘውን የአንድ ነጥብ ስምንት ቢልዮን ብር ገቢ እየተገባደደ ባለው ዓመት ወደ ሁለት ነጥብ ሶስት ቢልዮን ብር ማሳደግ መቻሉን የገለጹት ዶክተር አብዲ፤ በመጪው በጀት ዓመትም የገቢውን መጠን ወደ አራት ቢልየን የማድረስ እቅድ ይዘው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

የባቡር አገልግሎት የሎጂስቲክስ ስራዎች ላይ ብቻ ሳይሆን የሚጠበቅበት የሀገር ግንባታ ሂደት ላይም የራሱ የሆነ አወንታዊ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚገባው የገለጹት ዶክተር አብዲ፤ ከዚህም አኳያ ኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት ከተሞች የሚገናኙና የሚሰፉበትን መንገድም ጭምር እንደሚያመቻች ተናግረዋል፡፡

የባቡር ትራንስፖርቱ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ በኩል ባሉ ሠራተኞች የሚንቀሳቀስ ሲሆን፤ የባቡር መጓጓዣ አማራጩ ለሁለቱ ሀገራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ላይ አወንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሚገኝም ዶክተር አብዲ አመላክተዋል፡፡

የአገሪቷን የትራንስፖርት አቅም ከሦስት እጥፍ በላይ ያሳድጋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር መስመር ፕሮጀክት ግንባታ በ2004 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን መስከረም 25 ቀን 2009 ዓ.ም በለቡ ባቡር ጣቢያ መመረቁ የሚታወስ ነው፡፡ በሙሉ አቅሙ ሥራ ከጀመረም አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡

## በተሰራው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይመጣል፤ ይህንን ለመመከት አዲስ ዘመቻ ይኖራል። ስለሆነም በአለም አቀፍ ግንኙነት የሚዘጋና የሚያልቅ የቤት ስራ የለም። ኢትዮጵያን ወክለው በተለያዩ ሀገራት ያሉ አምባሳደሮች ይህንን ከግምት በማስገባት ለፈተናዎች ዝግጁ መሆን እንደሚኖርባቸው ገልጸዋል።

ዋናውን የአገር ፈተና በሁለት አመት ዘመቻ በመታገል ኢትዮጵያን አሻግረናል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ዜጎቿ በውስጥና በውጭ የዲፕሎማሲ ስራዎች ዘምተው በጋራ መስራት በመቻላቸው ችግሮችን ተሻግራለች። ይሁን እንጂ የቤት ስራችን አላለቀም፤ መልኩን እየቀየረ ይቀጥላል። በመሆኑም አምባሳደሮች ይበልጥ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብለዋል። በቀጣይ በሰብአዊ መብት፣ በታላቁ ሕዳሴ ግድብና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ አጀንዳዎች አሉ፤ የሚዘጋ ነገር አለመኖሩን በመገንዘብ በቅንጅት ተናበና ካለፉት ሁለት አመታት በበለጠ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ የስልጠናው አላማ የውጭ ስራዎችን ከኢትዮጵያ ተጠቃሚነት አንፃር በማገናዘብ የዲፕሎማሲ ስራ ለመስራት ያለመ ነው። ያለፉት ሁለት አመታት የፈተናና የሩጫ ጊዜ ነበር። በተሰራው ዲፕሎማሲያዊ ስራ ችግሮች እየተፈቱ ወደ መደበኛ አሰራር እየተመለስን ነው፤ በተለይም የውጭ ግንኙነት ለኢትዮጵያ ትልቅ ፈተና ነበር። ነገር ግን ሕዝቦቿ፣ የሰላም አስከባሪ ሀይሎችና ዲፕሎማቶች እልህ አስጨራሽና የተባበረ ዘመቻ ማካሄድ በመቻላቸው ፈተናዎች መፈታታቸውን ገልጸዋል።

ችግሮች በተጀመሩ በመጀመሪያው አካባቢ ብዙ ዋጋ ከፍለን ችግሮችን የማለዘብና የማስገንዘብ ዲፕሎማሲያዊ የዘመቻ ስራ ተሰርቷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በመገባደድ ላይ ባለው አመት ዲፕሎማሲያዊ ስራን ማዕከል አድርገን ተጉዘናል። በተለይ የወዳጅ ማብዛት፣ አጋር የማስፋት፣ የኢትዮጵያን ሁኔታ በማስገንዘብ ብሔራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ስራ ተሰርቷል። የአገርን ጥቅም ያስከበረና የተባበረ እንቅስቃሴ ማድረግ ተችሏል። መንግስት የሰላም አማራጭን ሁነኛ መንገድ አድርጎ በመያዝ ችግሮችን ለመፍታት በዲፕሎማሲ የታጀበ ከፍተኛ ንቅናቄ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ከፍተኛ ውጤትም እንደተገኘበትም ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

# "የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ማቅናት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኡስታዝ ካሚል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ከሁለት ዓመታት በኋላ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በአቶ ታገሰ ጫፎ የሚመራ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የልዑካን ቡድን ወደ መቀሌ መሄዱ ልዩ ደስታን ፈጥሮላቸዋል፡፡

የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ማቅናት ሰላምን ከማብሰር በዘለለ በወረቀት ላይ የሰፈረው የሰላም ስምምነት ተግባራዊነቱ ወደ መሬት መውረዱን፣ ለትግራይ ሕዝብ የሚደረገው ሰብዓዊ እርዳታ ከሪፖርት ባሻገር በተጨባጭ ምን እንደሚመስል እና የመሰረተ ልማቶችን ግንባታ መገምገም እንደሚጨምር የገለጹት ኡስታዝ ካሚል፤ በተጨማሪ የሕዝቡን ፍላጎት ለማወቅ እና ጥያቄውን ለማዳመጥ እድል እንደሚፈጥርም አመልክተዋል፡፡

ልኡካን ቡድኑ የሰላም ስምምነቱ ወረቀት ላይ በሰፈረው መሰረት በክልሉ ተግባራዊ ለማድረግ ያለው እንቅስቃሴ የማየትና የተፈጠሩ ክፍተቶችን ለማወቅና ለማስተካከል እንደሚረዳ ጠቁመዋል፡፡

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው አለመግባባት በስምምነት እልባት ማግኘቱ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውም ኃይል በንግግር ካልሆነ በቀር በጦርነት ማሸነፍ እንደማይችል እንዲሁም ሌሎችም ወደ ሰላም እንዲመጡ መንገድ ያሳየ ክስተት ነው ያሉት ኡስታዝ ካሚል፤ በደቡብ አፍሪካ የተደረገው የሰላም ስምምነት በር ከፋችና መላውን ሰላም ወዳድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስደሰተ እንደመሆኑ የአሁኑ የልዑካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ጉዞ ለመላ ኢትዮጵያውያንና ለውጭ ኃይሎች ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በተለያዩ አገራት የሰላም ስምምነት ተደርጎ ግማሹ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተግባራዊ የተደረገ፣ ግማሹ ደግሞ ያልተሳካበት ሁኔታ በመኖሩ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት ያሉት አቶ ኡስታዝ፤ ከዚህ አንጻር ግለሰቦችና ሚዲያዎች የነበረውን ቁስል ከሚያስታውሱና ጠላትነትን ከሚያባብሱ ነገሮች መቆጠብ አለባቸው ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ መንግሥትም መልሶ በመገንባትና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚያደርስበት ጊዜ ለአማራና ለአፋር ክልሎችም ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ኡስታዝ፤ ድጋፉን በአፋጣኝ እውን ለማድረግ ከዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ ለማግኘት ከሚደረገው እንቅስቃሴ በተጓዳኝ ክልሎችን በማስተባበር ያሉንን የውስጥ አቅሞች ለመጠቀም መጣር ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

እንደ ኡስታዝ ካሚል ማብራሪያ፤ አንዳንድ የዓለም መንግሥታት ርዳታ ለመስጠት የሚያስቀምጡት ቅደመ ሁኔታ ተገቢ አይደለም፡፡ አሁን ላይ ከሁሉም የሚቀድመው ለተራበው ምግብ፣ ለተጠማው ውሃ፣ ለታመመው መድኃኒት፣ ጨለማ ውስጥ ላለው ደግሞ ብርሃን ማቅረብ ነው፡፡ ቅድመ ሁኔታዎች በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚመጡ ናቸው፡፡ አሁን የተጀመረው ግንኙነት ወደ ሕዝብ ወርዶ የነበረውን ወንድማዊ ፍቅርም ወደ ቦታው መመለስ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም የተሰጠን ቁርጠኝነት ያሳየ ወሳኝ ጉዞ!

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ እሴቷም ከፍ ያለ ስም አላት። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከምትጠቀስባቸው ገናና ታሪኮቿ በተጓዳኝ በመቻቻል፣ እንዲሁም በፍቅርና በሰላም አብሮ የመኖር እሴቷ ለሌሎች ምሳሌ ሆና የምትቀርብ ጥንታዊት አገር ናት። በዚህ ረገድ በኃይማኖቶች ተቻችሎ የመኖር እሴቷ ለብዙዎች አብነት ሆኖ የሚቀርብ ሲሆን፤ ከ80 በላይ የሆኑት ብሔር ብሔረሰቦቿ በዘመናት የታሪክ ሂደት ውስጥ ገንብተው የያዙት ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶቻቸው እንደ አገር በአንድነት ፀንተው ለመኖር ከፍ ያለ ድርሻ አለው፡፡

በተለይ ኢትዮጵያውያን ችግሮቻቸውን አሸንፈው የሚሻገሩባቸው የሽምግልናና መሰል ግጭቶችን በእርቅ ፈትቶ ሰላምን የማጽኛ እሴቶቻቸው፤ ትናንትም ሆነ ዛሬ በውስጥም በውጪም ገፊ ምክንያት የሚገጥሟቸውን አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰላም ተነጋግሮ የመፍታት አቅም ፈጥረውላቸዋል። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ እንደ አገር በብዝሃነት ደምቃ፤ ኢትዮጵያውያንም እንደ ህዝብ በሕብር አጊጠውና ጠንክረው አነድነታቸውን አጽንተውና ለችግሮቻቸው ሳይንበረከኩ ዛሬ ላይ መድረሳቸው፡፡

ይህ ባህላዊና ማህበራዊ እሴታቸው ታዲያ፣ ከማህበራዊ አውዱ ባሻገር ወደ ፖለቲካው አውድ እንዲሰርጽና በፖለቲካው መስክ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በእነዚህ እሴቶች እልባት ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎችም ሲሰሩ ቆይተዋል። በዚህም የፖለቲካ አለመግባባቶች ወደግጭት ሳያመሩ መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ የተቻለባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። አለመግባባቶቹ ገፍተው ወደ ግጭት ካመሩም በኋላ አገርና ሕዝብ በጦርነት ውስጥ ሲጎዱ እንዳይኖሩ በእነዚሁ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች ታግዞ፤ በሕግና አሰራር ተደግፎ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት የተቻለባቸው አጋጣሚዎችም አሉ፡፡

ከ2010ሩ አገራዊ ለውጥ ማግስት እንደ አገር የገጠመውን ችግር ከመፍታት አኳያም እነዚህ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሽምግልናውም፣ በኃይማኖታዊ አስተምህሮውም፣ በባህላዊ መስመሩም በብዙ ተሰርቷል። ይሁን እንጂ ይሄ ጥረት ውጤት የሚያመጣው። በዚህ ረገድ በመንግስት በኩል የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሰላም እናቶችን፣ የኃይማኖት አባቶችን በተደጋጋሚ የሰላም መልዕክተኛ አድርጎ ቢልክም፤ ጥረቱ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ አለመግባባቱ ወደ ግጭትና ጦርነት አምርቷል፡፡

የአገርን ሕልውና ለማስጠበቅ መንግስት ተገድዶ ወደ ጦርነት ከገባ በኋላም ቢሆን፤ ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን፣ ተደጋጋሚ የተናጠል ተኩስ አቁሞችን ሲያደርግ ቆይቷል። በመጨረሻም ከብዙ ዋጋ መክፈል በኋላ ጥረቱ ፍሬ ያፈራበትን የሰላም ንግግር ማድረግ እና የጋራ ስምምነት መፈረም ተቻለ። ይሄን ተከትሎም መንግስት እንደ መንግስት ለሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት ከእርሱ የሚጠበቀውን ሁሉ በግንባር ቀደምትነት ሲከውን ቆይቷል። ከሰብዓዊ ድጋፍ እስከ መልሶ ግንባታ ያሉ ተግባራትን በቁርጠኝነት ከውኖ ውጤት አስገኝቷል። ይሄው ተግባሩም ሰሞኑን በኬንያ በተካሄደ ግምገማ ላይ ምስጋናን አስችሮታል። በሕወሓት በኩልም ያለው መልካም ጅምር የሚበረታታ ስለመሆኑም በዚሁ መድረክ ተነስቷል፡፡

ከኬንያው የጋራ ውይይትና ግምገማ ማግስት በኢትዮጵያ በኩል የሰላም ስምምነቱን ዘላቂ ከማድረግ አኳያ እንደ መንግስት የነበሩ ሂደቶችን ቁጭ ብሎ ገምግሟል። በዚህም አበረታች ውጤት እየታየ ስለመሆኑ ተመላክቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ "የናይሮቢ ሁለተኛውን ውይይት ተከትሎ የሰላም ሂደቱን ገምግመናል። እንደ ግምገማችን የሰላም ስምምነቱ የትግበራ ሂደት ተስፋ ሰጪ ነው። አሁንም ለሰላም ባለን ቁርጠኝነት ጸንተናል።" ሲሉ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው የገለጹበት አግባብ ይሄንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡

መንግስት የግምገማውን ውጤት ከመግለጽና በቀጣይም ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ከመግለጽ ባለፈ፤ ይሄንኑ ቃል ወደተግባር የቀየረ እና እንደ አገር የተጀመረውን የሰላም ሂደት ወደ ሌላ አዲስ ምዕራፍ የቀየረ መንገድን ጀምሯል። ለዚህ ጉዞ ስኬት እውን መሆን ደግሞ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሠ ጫፎ የሚመራ እና የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባላትን ያቀፈ የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ የልኡካን ቡድን ትናንት ወደ መቀሌ አቅንቷል፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዳስታወቀው ደግሞ፤ የልኡካን ቡድኑ ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ መቀሌ የተጓዘ የመጀመሪያው የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ልኡክ ሲሆን፤ የልኡካን ቡድኑ ወደ መቀሌ ያቀናው የሰላም ስምምነቱን የትግበራ ሂደት ለመቃኘትና በስምምነቱ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች በታቀደው መሠረት እንዲፈጸሙ ለማድረግ ነው። ይህ ደግሞ በአንድ በኩል የሰላም ስምምነቱ በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አጉልቶ ያሳየ ሲሆን፤ በሌላ በኩል መንግስት ዛሬም ለዘላቂ ሰላም ያለውን የማይዋዥቅ አቋም እና ስለ ሰላም ሲል የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍሎ ምን ያህል ርቀት መጓዝ እንደሚችል ለሁሉም ወገን ያረጋገጠበት ተግባር ነው !


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# አገራዊ መግባባት ለዘላቂ ሰላም

**በክብረአብ በላቸው**

የተለያዩ አገራት በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ አገራዊ ችግሮችን/መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ያጋጠሙ አለመግባበቶችን/አካታች በሆነ አገራዊ ውይይት መፍታት ችለዋል። በዚህም ዘላቂ ሠላም በመስፈን የተሳካ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖላቲካዊ ለውጥ ማምጣት ችለዋል።

ለአብነት ያህል ደቡብ አፍሪካን መጥቀስ ይቻላል። ዜጎቿ አገሪቱን እንደአገር የህልውና አደጋ ውስጥ ጥሎ የነበረውን ችግር ይቅርታ እና እርቅን መሰረት ባደረገ አገራዊ ውይይት በአገራቸው ጉዳይ ተገልለው የነበሩ ቡድኖችን ጭምር እንዲደመጡ እድል በመስጠት ችግሮቻቸውን መፍታት ችለዋል።

ይሄ ደግሞ ለአገራችን ኢትዮጵያ እንደ አንድ አብነት ሊወሰድ የሚችል ተግባር ነው። ምክንያቱም አገራዊ ውይይቶች በተለይ በክልሎች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ከብዙ በላድርሻ አከላት ጋር ተወያይቶ ለመፍታት ውጤታማ ይሆናሉ። ባለድርሻ አካለት አገራዊ ውይይት በሚጠሩበት ጊዜ አላማው ብዙውን ጊዜ ፖለቲካ ተሳትፎን ማስፋት እና በሌለ መልኩ ለተገለሉ ቡድኖች ባለቤትነት መስጠት ነው፡፡

ይህ የበለጠ አካታች ሂደት እና የተሻለ ዘላቂ ውጤት ለማምጣት መንገድ ይከፍታል። ነገር ግን አገራዊ ውይይቶች አንዳንዴ በልሂቃን ለብሔራዊ ዓላማ የፖለቲካ ህጋዊነትን ለማግኘት ወይም ለማስመለስ እንደ መሳሪያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህም የለውጥ አቅማቸውን በመገደብ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚደረግ ምክክር ግን ከእንደዚህ አይነት ፍላጎት በጸዳ መልኩ በዕውነት ለይ በተመሰረተ ግንኙነት እና ስሜትን ተቆጣጥሮ ቁጭ ተብሎ በጥሞና በመነጋገርና በመደማመጥ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፤ እርስ በእርስ የሚነጋገሩበት፤ የሚመካከሩበት እና የጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ነው።

አገራዊ ምክክር ደፍሞ በዚህ መልኩ ሲከወን ከአሸናፊነትና ተሸናፊነት ስሜትና እልህ ነጻ በሆነ መንፈስ ሁሉም/አገርና ህዝብ/ አሸናፊ የሚሆኑበት የፖለቲካ ምህዳር መፍጠር የሚያስችል ነው። ዘላቂ ሰላምና መግባባትን በመፍጠር ዜጎችን ከግጭትና ግጭት ከሚፈጥረው ኪሳራ ለመታደግ ያስችላል።

> **አገራዊ ምክክር አለመግባባቶች ወደ ግጭት ከማምራታቸው በፊት መከላከል የሚያስችል ሲሆን፤ በዜጎች መካከል አዲስ ማህበራዊ ውል እስከ መፍጠር የሚደርስ ዓላማ ሊኖረው ይችላል**

አገራዊ ምክክር በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ የተለያየ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ ባሕል፣ ወግና ልማድ ወዘተ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን አካታች በሆነ ስርዓት ቁጭ ብለው ላለመግባባታቸው ምክንያት በሆኑ ጉዳዮቻቸው ዙሪያ የሚመካከሩበትና ወደ መግባባት የሚሸጋገሩበት ሂደት ነው።

አገራዊ ምክክር አለመግባባቶች ወደ ግጭት ከማምራታቸው በፊት መከላከል የሚያስችል ሲሆን፤ በዜጎች መካከል አዲስ ማህበራዊ ውል እስከ መፍጠር የሚደርስ ዓላማ ሊኖረው ይችላል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የሕብተሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካ እና የሀሳብ መሪዎች መካከል እጅግ መሰረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሳይቀር የሀሳብ ልዩነት እና አለመግባባት እንዳለ ይታመናል። ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት አገራዊ የምክክር ኮሚሽን በአዋጅ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል።

ተስፋ የተደረገው አገራዊ ምክክሩ የተሻለ አገራዊ አንድነት ለመገንባት በሂደትም የመተማመን እና ተቀራርቦ የመስራት ባህልን ለማጎልበት እንዲሁም የተሸረሸሩ ማህበራዊ ዕሴቶችን ለማደስ የሚጠቅም ነው፡፡

አገራዊ ምክክሩ ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ያለው እንዲሆንም ኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ተሰይመውለት ገለልተኛ እና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ግለሰቦች እንዲመራ ተደርጓል። ተጠያቂነታቸውም ገለልተኛ ለሆነ አካል እንዲሆን ተደርጓል።

ምክክሩ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት፣ መተማመንን ለማጎልበት፣ እንዲሁም በመንግስት እና በህዝብ መካከል መልካም ግንኙነትን ለመፍጠር የሚያስችል አዲስ አስተሳሰብና ለአስተሳሰቡ የሚገዛ ማህበረሰብ መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ ነው።

የቆዩ አለመግባባቶችን ጨምሮ አሁን ላይ የሚስተዋሉ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት በመፍታት፣ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ለሚደረገው ጉዞ የውይይት ባህልን ማዳበር እና ወቅታዊ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ይረዳል።

ሰላምን በማረጋገጥ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ መደላድል ከመፍጠር በተጨማሪ አገራዊ መግባባት በመፍጠር ጠንካራና ቅቡልነት ያለው አገረ መንግስት ለመገንባት የሚያስችል መሰረት ለመጣልም የተሻለ እድል መፍጠር ያስችላል። ለዚህም ሲባል ኮሚሽኑ የውይይት አጀንዳዎችን ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በመምከር በመምረጥ ላይ ይገኛል።

ላለመግባባቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በጥናትና በሕዝባዊ ውይይቶች በመለየት፣ በተለዩት አጀንዳዎች ላይ አገራዊ ምክክሮችን በማካሄድ፣ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ እና ለተግባራዊነቱም የመከታተያ ስርዓት በመዘርጋት ለአገራዊ መግባባት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተልዕኮ አድርጎ እየሰራ ነው። በዚህም በ2017 ዓ.ም በአገሪቱ እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባት ተፈጥሮ የማየት ርዕይ አስቀምጧል፡፡

በዚህ ረገድ የተሳካ ብሄራዊ ውይይት ማድረግ አገሪቱ ለምታደርገው የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞ መደለደልን ከመፍጠር በዘለለ ጠንካራ አገረ መንግስት ለመገንባት ሚናው የጎላ ነው። በመሆኑም ለአሳታፊነቱ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያሻል። አካታች፣ ግልጽ እና ተአማኒነት ያለው የምክክር ሂደት እንዲኖረው ማድረግም ተገቢ ነው፡፡

ይህ ሲባል፣ ሰፊ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ አካላት፤ ለምሳሌ አርሶ አደሮችን፣ አርብቶ አደሮችን፣ የሲቭክ ማህበራት፣ ሴቶችና ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የሃይማኖት እና ባህላዊ መሪዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ መንግስት እና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማሳተፍ ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ብሄራዊ ውይይቱ የታለመለትን ዓላማ ማሳካት ስለሚችል፤ ለዚህ ዓላማ መሳካት የሁሉንም በላድርሻ አካለት ጥረት አስፈላጊ ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# ዘላቂ እልባት የሚሻው የሲሚንቶ ጉዳይ

**ታምራት ተስፋዬ**

በኢትዮጵያ በየዓመቱ ስለ ሲሚንቶ ችግርና እጥረት እንዲሁም የዋጋ መወደድ ይወራል። ይመከርበታል። ዛቻ የተቀላቀለበት አቅጣጫም ይሰጥበታል። ይሁንና ችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሲያገኝ ሳይሆን፤ የምርት ስርጭት ሒደቱ ሲተረማመስ እና የባሰ ምስቅልቅል ውስጥ ሲገባ የሚስተዋል፤ ይልቁንም ወግ የሌለውና ሽፍጥ የሚታይበት፣ ሁሌም ቢወቅጡት እንቦጭ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡

እናም የሲሚንቶው ኢንዱስትሪ መሰል ቅርቃር ውስጥ ሲባዝን ‹‹ለምን እንዲህ ይሆናል››? በሚል ኃላፊነት የሚወስድ የለም። ሁሉም ‹‹ከደሙ ንፁህ›› ነን ባይ ነው። አምራቾች ‹‹የውጭ ምንዛሪ የሚሰጠን አጣን›› ሲሉ፤ አከፋፋዮች እና ቸርቻሪዎች ‹‹ከተመዘገብን ዓመት ሞላን፣ ይሁንና ወረፋ አልደረሰንም›› የሚል ሰበብ ይደረድራሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ገዢው ወይንም ተጠቃሚው በሚደርስበት የተደራረበ ችግርና ጫና ምክንያት ‹‹ኧረ የመፍትሔ ያለህ›› የሚል ምሬቱን ሲገልፅ ይሰማል፡፡

ይሁን እንጂ የሲሚንቶ ገበያ ከዓመት ዓመት በዚህ መልኩ በችግር ላለመላቀቁና እጅ ከወርች ካሰረው አዙሪት መላቀቅ ላለመቻሉ የተለያዩ ምክንያቶች ይዘረዘራሉ። ለአብነት፣ የግንባታዎች መበራከት እና ከአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን ጋር የተያያዘው ችግር አንዱ ነው። ምርቱ ከፋብሪካው አንስቶ ተጠቃሚው እጅ እስኪገባ ድረስ ያለው የግብይት ሰንሰለት ረዥም መሆንም ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው። ያልተገባ ጥቅም የማግኘት ፍላጎት/ስግብግብነት እንዲሁም የኢኮኖሚ አሻጥርን አይነት ጉዳዮችም በተደጋጋሚ የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡

አንድም ከብቃት ማነስ ሌላም ከጥቅም ተጋሪነት የሚመነጭ የቁጥጥር መላላት እንዲሁም በሲሚንቶ ፋብሪካዎች ውስጥ ባሉ ጥቂት ጡንቻማ ግለሰቦችና ከእነሱ ጋር የጥቅም ትስስር ባላቸው አካላት የሚፈጸሙ ህገ ወጥ ተግባራትም ለሲሚንቶው ቀውስ ምክንያት ተብለው ከሚዘረዘሩ ችግሮች ተርታ የሚያሰልፏቸውም ብዙዎች ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ ለሲሚንቶ ምርትና ስርጭት መዛባት ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱት መሰል ችግሮች መካከል አንዱና ምናልባትም ዋነኛው በሙስና የተዘፈቁ የመንግስት ባለስልጣናት ስውር እና ረጅም እጅ ስለመሆኑም የበርካቶች እምነት ነው፡፡

ይሄን የሚሉ ወገኖች ደግሞ በቅርቡ የተገለጠውን አንድ ሃቅ አንድ ብለው እንደማሳያ ይጠቅሳሉ። ይሄም ባለንበት የታህሳስ ወር መጀመሪያ የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት የኮንስትራክሽንና ሎጂስቲክስ ምክትል ዳይሬክተር ተስፋዬ ደሜና አራት የአገልግሎቱ ሰራተኞች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ነው። በዚህ ረገድ ከፍትህ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃም፣ ግለሰቦቹ በአገልግሎት ስም 29 ሺ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ከሁለት ፋብሪካዎች ገዝተው ለግለሰቦች በመሸጥ ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው በማዋል የተጠረጠሩበት የሙስና ተግባር መሆኑን ያመላከተበት ማሳያ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በማድረግ ላይ የምትገኝ አገር እንደመሆኗ፤ ሲሚንቶ በሁሉም መስክ በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፉ የምጣኔ ሀብት አንቀሳቃሽ ሞተርና የበርካቶች የስራ ዋስትና የዕለት ጉርስ ምክንያት ነው። ይሕ እንደመሆኑ ታዲያ የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት በአግባቡ መመራት ይኖርበታል። የሲሚንቶው ገበያ ሰላም ካላገኘ የሚበላሸው ብዙ ነው። የሲሚንቶ ግብይት መስተጓጎል፣ የስርጭቱ በሕገ ወጦችና በደላላዎች መመራት እንዲሁም በስግብግብ ነጋዴዎች መከዘን በአገር ላይ የሚያስከትለው ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡

ለአብነት፣ በግንባታው ዘርፍ የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው የነበሩ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ያለ ስራ እንዲባዝኑ፣ አምራች ጉልበታቸው ያለ አግባብ እንዲባክን ያደርጋል። ሌሎች የግንባታ ቁሶችን በማቅረብ የሚተዳደሩ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ስራም ይታወካል። በርካታ ለሕዝብ አገልግሎት ተብለው የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ባሉበት ለመቆም እንዲገደዱ እና ተስተጓግለው መጠናቀቅ ባለባቸው ጊዜ መጠናቀቅ አልሆን እንዲላቸው ምክንያት ይሆኗል፡፡

መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት የሲሚንቶው ቀውስ ‹‹ችግሩ ምን ይሆን›› በሚል ሲጠየቅ፤ ‹‹የመለዋወጫ ችግር ነው፣ ደላሎች የፈጠሩት ሰው ሠራሽ እጥረት ነው፣ የኢኮኖሚ አሻጥር ነው›› የሚል ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል። ውጤቱ በሚጠበቀው ልክ ባይሆንም መፍትሄ ያላቸውን መመሪያ እና የአሰራር ደንቦችን ማውጣት ጨምሮ የተለያዩ እርምጃዎች ሲወስድም ተስተውሏል፡፡

ለአብነት፣ ሐምሌ 2014 ዓ.ም የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሲሚንቶ ዋጋን የሚቆጣጠርና በሚኒስቴሩ የሚተገበረው መመሪያ በማውጣት ገበያው ላልተወሰነ ጊዜ በነጻ የገበያ ዋጋ ላይ ተመስርቶ እንደሚወሰን ገልፆ ነበር። በመስከረም 2015 ዓ.ም ደግሞ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአገሪቱ ያለውን የሲሚንቶ ምርት የዋጋ ንረት ለመግታት አዲስ የሲሚንቶ ዋጋ ደንብ ማውጣቱን አስታውቋል። ይህም ከአንድ ዓመት በፊት ከወጣው እጅግ በጣም የራቀ ነው። የነፃ ገበያ ኢኮኖሚውን የሚወስን ነበር።

መንግስት ለችግሩ ፍቱን መፍትሄ መስጠት እንዳልቻለ ያሳያል። ሂደቱም ለችግሩ ዘላቂ ከመስጠት ይልቅ አለባብሰው ቢያርሱ ሆኖበት ችግሮችን እየተከተሉ ጊዜያዊ መፍትሄ መስጠት ላይ መጠመዱን ያሳያል። ምክንያቱም ችግሩን ለማቃለል በሚል በየጊዜው መመሪያዎችን ሲገለባብጥ ከመቆየቱም በላይ፣ ‹‹ከዚህ በላይ ሽያጭ ሲያከናውን ያገኘሁትን አልምረውም አይቀጡ ቅጣት እቀጣዋለሁ›› የሚል ማስፈራሪያ እስከመስጠት ተሻግሮም ታይቷል። ይሁንና ለመፍትሄ የሚቀርቡ ሃሳቦች ሁሉ አንድ ኩንታል ሲሚንቶን ሁለት ሺህ ብር ከመሸጥ የመታደግ አቅም አልነበራቸውም፡፡

ምክንያቱም ከስድስት ወራት በፊት በመንግስት የወጣው የሲሚንቶ ስርጭት መመሪያ ህብረተሰቡን ከደላሎች፣ አስፈላጊ ካልሆነ የዋጋ ንረት፣ ከስርቆት እና ከቢሮክራሲያዊ አሰራር ለማላቀቅ ታስቦ የነበረ ቢሆንም፤ ባለፉት አምስት ወራት ትግበራ እንታየው ችግሮቹ እንዳልተቀረፉም። በአጠቃላይ የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋት እጥረቱን ለመቀነስ፣ እንዲሁም በግብይት ውስጥ ያለውን ረዥም ሰንሰለት ለመበጠስና በየጊዜው እንደ ችግር ለሚነሱ ጉዳዮች መፍትሔ ይሆናል የተባሉ ዕርምጃዎች ይሕ ነው የሚባል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም። መፍትሄ ተብለው የሚወሰዱ መድሃኒቶች ሁሉ በአብዛኛው ለማስታገሻ የሚረዱ እንጂ ህመሙን የሚያሽሩ አልነበሩም፡፡

ሆኖም ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉና አካሄዱ አላምር ያላቸው የተለያዩ የምጣኔ ሃብት ምሁራን አሁን ያለውን የሲሚንቶ ችግር ለመፍታት መፍትሔው አሁንም መንግስት እጅ መሆኑን ይገልጻሉ። ለዚህም ‹‹ገበያው ከፖለቲካ ንክኪ መውጣት አለበት፣ እንደውም መንግሥት ከዚህ ወጥቶ ገበያውን ነፃ ቢያደርገው ገበያው ይስተካከላል›› የሚል እምነት እንዳላቸው በተደጋጋሚ ሲገለፁ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ለጉዳዩ እየተሰጠው ያለው ምላሽ ‹‹አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ›› አይነት ሆኖ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም ግራ የገባውን የሲሚንቶ ዋጋ ለማረጋጋትና ለመቆጣጠር ከጥቂት ወራት በፊት ያወጣውን መመሪያ ባሳለፍነው ሳምንት አጋማሽ ዳግም ሽሮ በሌላ ተክቶታል፡፡

በአዲሱ ውሳኔውም ሲሚንቶ በነፃ ገበያ ዋጋ እንዲሸጥ ብሏል። በዚህ ውሳኔ ላይ ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠበት ሲሆን፤ መግለጫውን የሰጡት የንግድ ስርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ፣ በሲሚንቶ ስርጭትና ግብይት ላይ ሲስተዋል የነበረውን ችግር ለመቅረፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 908/2014ን በመላ አገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡

በዚህም በርካታ ውጤቶችን ማስመዝገቡን የተናገሩ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውጤቶች መካከል የቆሙ የፌዴራልና የክልል የመንግስት ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ሂደታቸው መግባታቸው፣ የግብይት ሰንሰለቱ እንዲያጥር መደረጉ፣ ጠረፍ የሚባሉ አካባቢዎች በመመሪያው አማካይነት የሲሚንቶ አቅርቦት እንዲያገኙ መደረጉ፣ የፋብሪካዎችን ያልተገባ ጭማሪ ማስታገስ መቻሉ፣ ትላልቅ የግል የግንባታ ፕሮጀክቶችና ሪል እስቴቶች በቀጥታ ከፋብሪካዎች ሲሚንቶ እንዲያገኙ መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡

በአንጻሩ በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የሲሚንቶ ምርትና ምርታማነት መቀነስ፣ እስከ መስከረም 20 2015 ድረስ ከሁለት ፋብሪካዎች ውጪ ስምንት ፋብሪካዎች ሽያጭ አለመፈጸማቸው፣ የተመረተው ሲሚንቶም በአግባቡ ያለመሰራጨት ችግር እንደነበር፣ የአንዳንድ ክልል ፕሮጀክቶች የሲሚንቶ ፍላጎት በአግባቡ ተጠንቶ እና ተደራጅቶ ለሚኒስቴሩ በወቅቱ አለመላክ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ቸርቻሪዎችን በመተካት ስርጭት እንዲያደርጉ የተመረጡት የልማት ድርጅቶች በቂ እና ተደራሽ የስርጭት ማዕከል ያለመኖር ችግሮችን መስተዋላቸውን ዘርዝረዋል፡፡

አያይዘውም፣ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሌላ መመሪያ መዘጋጀቱን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአዲሱ መመሪያ መሠረትም በኬላዎች አካባቢ በሲሚንቶ ምርት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ቁጥጥር መነሳቱ፣ ቸርቻሪዎችንና አከፋፋዮችን መምረጥ የፋብሪካዎች ኃላፊነት እንዲሆን መደረጉ፣ ያለደረሰኝ ምንም አይነት ግብይት እንዳይካሄድ መደረጉ፣ ከፋብሪካዎች የሚወጣ ማንኛውም የሲሚንቶ ምርት በቂ ሰነድ ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በፋብሪካዎች በር ላይ የሚደረገውን የሲሚንቶ ሽያጭ ዋጋ የመወሰን ስልጣኑን በአዲሱ መመሪያ ይዞ ቢቀጥልም፤ በየአካባቢው የሚኖረውን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ የመወሰን ኃላፊነት ግን ወደ ፋብሪካዎች እንዲተላለፍ አድርጓል። ሆኖም መንግስት የሲሚንቶ ምርት ከፋብሪካ ለተጠቃሚዎች የሚቀርብበት ሂደት በተገቢው ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰራ ታውቋል። በዚህም በመንግስት የሚከናወነው የቁጥጥር ስራ የሲሚንቶ ምርትን ‹‹ነጻነትን›› የሚያግድ አይሆንም ተብሏል።

ዋናው ነጥብ ግን በወራት ልዩነት ሚኒስቴሩ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰበትን ምክንያት ለማወቅ ቢያስቸግርም፣ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ አይነቱ ተግባር ግን የአገሪቱ የሲሚንቶ ኢንዱስትሪ የገባበትን ቅርቃር ግልፅ አድርጎ የማስመልከት አቅሙ ግዙፍ ነው። በእርግጥ ቀደም ሲል የግብይት ሥርዓቱን በመንግስታዊ መዋቅር ለመምራት የተደረገው ጥረት የተሳካ፣ የሕዝቡን ችግር ያቃለለ ሥራ ነበር ለማለት የሚያስደፍር ውጤት አልታየም። የሲሚንቶ ምርት በመንግሥት መዋቅሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ እየተመራ ዋጋው መናሩ አልቀረም። የሕገ ወጦች መጠቀሚያ ከመሆንም አልዳነም።

ከዚህ አንጻር አሁን ላይ ማሻሻያ መደረጉም እሰየው የሚያሰኝ ቢሆንም፤ አሁንም ቢሆን ሲሚንቶ በነፃ ገበያ እንደ ቀድሞው እንዲገበያይ መወሰኑ ብቻውን መፍትሔ ይሆናል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በመሆኑም ሕግ፣ ደንብ እና መመሪያ ከማውጣት ባለፈ ለውጤታማ ተፈፃሚነቱ በቂ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

አሁንም ቢሆን ቀደም ሲል የግብይት ሥርዓቱን በመንግስታዊ መዋቅር ለመምራት ሲሞከር በሂደቱ የተገኘው ውጤት ምንድን ነበር? ከትርፉና ከኪሳራው የቱ በልጦ ታየ? ድክመቱስ የቱ ጋራ ይበልጥ ተስተዋለ? ብሎ መፈተሽ፤ ለስኬታማነቱ መጓደል ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን መለየት እና መቀመር የግድ ይላል። የሰሞኑ ውሳኔ ገበያውን ምን ያህል ያረጋገዋል የሚለውን ወደፊት የምናየው ይሆናል። ይሑንና ‹‹ሁኔታው ለእኔ ተመችኝ" እንዳለው ሙዚቀኛ እንዳይሆንና የሲሚንቶ ገበያው በሕገ ወጥ ነጋዴዎችንና ደላላዎች እንዳይዘወር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

በተለይ የምርት አቅርቦት ሰንሰለቱን ከደላሎች ጣልቃ ገብነት ለማላቀቅ፣ በጥቁር ገበያ ዘዋሪዎች አማካይነት ፈር የሳተውን ግብይት ለማስተካከልና መልክ ለማስያዝ መንግሥት በአንክሮ ሊሰራ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ከሌብነትና ከዘራፊነት ጋር ስማቸው የማይነሳ ህጋዊው የንግዱ ማኅበረሰብ በነፃነት ሥራቸውን የማከናወን መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የግብይት ሥርዓቱን የሚያተራምሱ ደላሎችን አደብ ማስገዛት፣ ምርት አንቀው የሚይዙትንም ሆነ የሚሰውሩትን በሕግ መቅጣት የግድ ይላል፡፡

ከሁሉ በላይ የአንድን ድርጊት ወይም ውሳኔ ተጠቃሚዎችን ‹‹beneficiary of an action›› ኖችን ለይቶ ማወቅና ማስወገድ ሊዘነጋ አይገባውም። እናም እዚህ አካባቢ በሚገባ መፈተሽና ፈጣን ማስተካከል ማድረግ ከተቻለ ሌላው ዕዳው ገብስ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ከሁሉ በላይ መንግስት በየጊዜው መመሪያ ከመገለባበጥ ጊዜ ወስዶ እና ጥናት ላይ ተሞርክዞ አጠቃላይ የሲሚንቶ የግብይት ሥርዓቱን ለማስተካከል የሚረዱ እርምጃዎችን ለመራመድ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ አሁንም በስመ ነፃ ገበያ ስም ሲሚንቶ በጥቂት ተዋናዮች እየተተራመሰ መቀጠሉ አይቀርም፡፡

በእርግጥ ግብይት እና ስርጭቱ መሄድ ባለበት መንገድ እንዲራመድ በማድረገ ረገድ መንግስት ብቻውን ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። ጉዳዩን ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው አይደለም። ሁላችንም በምን አገባኝ ስሜት የምናልፈው ሕገ ወጥ ሥራ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዋጋ የሚያስከፍለው እኛኑ ነው፡፡

በመሆኑም ሕጋዊ አሠራር ብቻ እንዲተገበር፣ ሕገ ወጥ ሥራዎች በፍጥነት እንዲታረሙ የጋራ ሚናችንን መወጣት አለብን። ለጋራ ተጠቃሚነታችን ስንል ሕግ፣ ደንብ እና መመሪያ አክባሪም አስከባሪም እንሁን። በጥቂቶች ስግብግብነት ብዙኃኑ ሕዝብ እንዳይጎዳ ተገቢ ሞራላዊ፣ ሕጋዊና ፖለቲካዊ ዕርምጃዎች ሲወሰዱም ተገቢን ድጋፍ መስጠት ይኖርብናል፡፡

> **የምርት አቅርቦት ሰንሰለቱን ከደላሎች ጣልቃ ገብነት ለማላቀቅ፣ በጥቁር ገበያ ዘዋሪዎች አማካይነት ፈር የሳተውን ግብይት ለማስተካከልና መልክ ለማስያዝ መንግሥት በአንክሮ ሊሰራ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ከሌብነትና ከዘራፊነት ጋር ስማቸው የማይነሳ ህጋዊው የንግዱ ማኅበረሰብ በነፃነት ሥራቸውን የማከናወን መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የግብይት ሥርዓቱን የሚያተራምሱ ደላሎችን አደብ ማስገዛት፣ ምርት አንቀው የሚይዙትንም ሆነ የሚሰውሩትን በሕግ መቅጣት የግድ ይላል**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ለበይነመረብ ተደራሽነት - በእውቀትና በመረጃ የበለጸገ ማህበረሰብ ሚና

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በበይነ መረብ በመጠቀም ወጪንና ጊዜን መቆጥብ፣ በፍጥነት ተደራሽ መሆን ዘመኑ የሚጠይቀው ወሳኝ ተግባር ሆኗል። ይህ የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በማቃለል በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በዓለም አቀፍ እንዲሁም በአፍሪካም በሚፈለገው ልክ ተደራሽ እንዳልሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። በዓለም ላይ 2ነጥብ 7 ቢሊዮን፣ በአፍሪካ ደግሞ 871 ሚሊዮን ሕዝብ ከበይነ መረብ ግንኙነት ውጭ ስለመሆኑም በቅርቡ በአዲስ አበባ በተካሄደው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ላይ ተጠቁሟል።

በጉባኤው ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በኢትዮጵያ ያለው የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከአምስት ዓመት በፊት ከነበረበት 19 ሚሊዮን፣ በአሁኑ ወቅት ከ30 ሚሊዮን በላይ መድረሱን አመልክተዋል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የበይነ መረብ ተደራሽነት እያደገ የመጣ መሆኑን የጠቆሙት የዘርፉ ባለሙያዎች፣ ተደራሽነቱ የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነና በትኩረትና በስፋት ሊሰራበት ይገባል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ምህንድስና ትምህርት ክፍል ኃላፊ አቶ ፊሊክስ ኢቴሳ ስለ በይነ መረብ /ኢንተርኔት/ በይነ መረብ /ኢንተርኔት/ ለመማር፣ ለምርምር እንዲሁም ለህብረተሰቡ የዕለተ ተዕለት እንቅስቃሴ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ እንደ ቅንጦት የሚታይ እንዳልሆነ ያመለክታሉ። በዚህ የዲጂታል ዘመን ካለ ኢንተርኔት በቴክኖሎጂ ሳይታገዙ መሥራት አዳጋች መሆኑንና በትኩረት ሊሰራበት እንደሚገባም ያስገነዝባሉ፡፡

እንደ አቶ ፊሊክስ ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ተደራሽነት በእጅጉ አናሳ ነው። የኢንተርኔትን ተደራሽነት ለማወቅ ኢንተርኔት የት የት አካባቢዎች አለ? መሠረተ ልማቱስ በሚገባ ተደራሽ ሆኗል ወይ? በየቦታው የቴሌኮሙኒኬሽን ማዕከላት አሉ ወይ? ምን ያህል ሰው ተጠቃሚ ሆኗል የሚሉት ሁሉ መታየት ይኖርባቸዋል።

ማህበራዊ ድረገጽ (ፌስ ቡክ)፣ ዩቲዩብና የመሳሰሉት የመረጃ መለዋወጫ ዘዴዎችስ (ፕላት ፎርሞች) ምን ያህል ተጠቃሚዎች እንዳሏቸው ለይቶ ማወቅ ይገባል። ዘመናዊ /ስማርት/ የስልክ ቀፎ ያለውም ቢሆን ጥቂት ሰው ነው። እንደ ሀገር የተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ቴክኖሎጂ ከተጀመረ አንስቶ ኢንተርኔት ፍጥነቱ እያደገ አምስተኛ ትውልድ (5ጂ) ኔትወርክ ላይ የደረሰ ቢሆንም፣ የኢንተርኔት ፍጥነቱ ግን አሁንም በጣም አነስተኛ ነው።

‹‹አሁን ባለው ሁኔታ ኢንተርኔት እየተጠቀምን ነው ማለት አይቻልም›› ያሉት አቶ ፊሊክስ፤ የኢንተርኔት ተደራሽነት የሚለካው በመሠረተ ልማቱ መዘርጋት ብቻ ሳይሆን፣ በፍጥነቱም ነው ብለዋል። የኢንተርኔት ተደራሽነትን ለማስፋፋት በተግዳሮት ከሚጠቀሱት ዋንኛና መሠረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ስለዲጂታል ቴክኖሎጂ ያለው ግንዛቤ አነሳ መሆኑም አንዱ ነው ይላሉ፡፡

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽን ሳይንስ ባለሙያው አቶ ጥላሁን ሽፈራው የኢንተርኔት ጥቅሙ የገባቸው አንዳንድ የዓለም ሀገራት እንደ አንድ የሕይወት አካል አድርገው በመውሰድ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ይናገራሉ። የቴክኖሎጂ መኖር ብቻውን ውጤታማ እንደማያደርግም ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል ያሉት አቶ ጥላሁን፣ አጠቃቀምና የሚተዳደርበት ሁኔታ ሊታይ ይገባል ነው ያሉት። ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም መሠረተ ልማት መሟላት እንደሚኖርበት፣ ተጠቃሚውና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ተጣምረው መሄድ እንዳለባቸው ያመለክታሉ። የኢንተርኔት ተደራሽነትን ለማስፋፋት በቅድሚያ ኢንተርኔት አስፈላጊ እንደሆነ ሊታመንበት ይገባል ይላሉ፡፡

የኢንተርኔት ተደራሽነት የኮምፒዩተር ተጠቃሚነት ሰዎች እውቀት ላይ መሠረት ያደረገ እንደሆነ ያመላከቱት አቶ ፊሊክስ፤ በሀገሪቱ ያለው የዲጅታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በጣም አናሳ መሆኑን ይጠቁማሉ። መሠረታዊ የኮምፒዩተር እውቀት የሌላቸው ዜጎች በትምህርት ቤቶች፣ በእስር ቤቶች፣ የወትድርና ቦታዎችና በሌሎች መስኮች መኖራቸውንም ያመለክታሉ።

> **አሁን ያለንበት የመረጃ ጊዜ ነው፤ በመረጃ የበለጸገ ህብረተሰብ መገንባት ያስፈልጋል። ቴክኖሎጂ ማምጣት ላይ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ ላይ መሥራትም ይገባል። በመረጃ የበለጸገ በእውቀት የሚመራ ህብረተሰብ ማምጣት ከተቻለ ህብረተሰቡ ራሱ ኢንተርኔትን ይጠይቃል፤ ቴክኖሎጂን ይፈጥራል**

በትምህርት ቤቶች አካባቢ ያለው ተደራሽነት በጣም አናሳ እንደሆነም አመልክተው፣ የኢንተርኔት ተደራሽነት ተስፋፍቶ ማህበረሰብ የትም ቦታ ላይ በስፋት መጠቀም መቻል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ፊሊክስ ማብራሪያ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብንመለከት መሠረተ ልማት ተዘርግቶ፣ የዳታ ማዕከላት ተገንብተው፤ መጠቀሚያ መሳሪያዎቹ በውድ ዋጋ ተገዝተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። ሆኖም ግን እነዚህ ማዕከላት በባለሙያ እንዲመሩ ባለመደረጉ ጉዳት ይደርሳል። ቴክኖሎጂው ብዙ ጥቅም ሳይሰጥ አገልግሎቱ ይቋረጣል። ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ጥቅም ላይ እንዲውል ሁሉም የየድርሻውን መወጣትና ትኩረትም ማግኘት አለበት፡፡

ሀገሪቷ ወደኋላ እንድትቀር ያደረጋት የዲጂታል ቴክኖሎጂ እጥረት መሆኑን ነው አቶ ፊሊክስ የሚጠቁሙት። የዓለም ሀገራት የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ኢንተርኔት መጠቀም የግድ እንደሆነም ያስረዳሉ። ለአብነት የጃፓንን ልምድ ብንመለከት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በቀጥታ ትኩረት ያደረጉት ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ ላይ ነው የሚሉት አቶ ፊሊክስ። ጃፓኖች ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ መሠረት የሆናቸው በየትኛውም መስክ በግብርናም ሆነ ጤና ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ላይ ትኩረት አድርገው በመሥራታቸው ነው ይላሉ። በተለይ ሀብት ሳይኖራቸው ከባህል ጋር የተዋሃደ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ኢንተርኔት ልክ እንደ ትምህርት ቤት ሁሉ ተደራሽነቱ በገጠሪቱ ሀገሪቱ ክፍል እንዲስፋፋ በማድረጋቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢንተርኔት ተደራሽነት ለማስፋት የዓለም ሀገራትን ተሞክሮ ወደ ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ማምጣት ይገባል ብለዋል።

አቶ ፊሊክስ በዚህ አራት ዓመት በመንግሥት ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ ስለ ኢንተርኔት ያለው ግንዛቤ በጣም ተለውጧል ሲሉ ገልጸው፣ መንግሥትም ትኩረት ሰጥቶ የኢንተርኔት ተደራሽነት ላይ እየሰራ መሆኑንና በዚህም ለውጦች መምጣታቸውን አመላክተዋል። ለአብነት ባንኮች በኢንተርኔት ግንኙነታቸውን እያሰፉ የምንመለከትበት ሁኔታ ለውጥ መኖሩ ማሳያ ይላሉ፡፡

ለኢንተርኔት ተደራሽነት እንደ ተግዳሮት የተቀመጡትን ችግሮች መንግሥት ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ነው አቶ ፊሊክስ ያመላከቱት። ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትኩረት በመስጠት ከተሰራና በፖሊሲ ከተደገፈ መሠረተ ልማቱ እየሰፋ ይመጣል ባይ ናቸው። እንደ መንግሥት ለኢንተርኔት ከፍተኛ በጀት ተመድቦ መሥራት እንዳለበት አመላክተው፤ "ኢንተርኔትን ተደራሽ ለማድረግ የተዘረጋ መሠረተ ልማትና ተጠቃሚው ካልተመጣጠነ ኢንተርኔትን አንጠቀም እንደማለት ነው። ለምሳሌ ጎግል ወይም ዩቲዩብ ቢጠፉ ኢንተርኔት አንጠቀም ማለት ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ በራሳችን የፈጠርናቸው ፕላት ፎርሞች ስለሌሉ ነው" ብለዋል፡፡

አቶ ፊሊክስ በሌላ በኩል ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ገብተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲደርግ በቀጥታ እንደመጡ ከመጠቀም ከሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ እና ባህል ጋር አቀናጅቶ የመጠቀም ችግር መኖሩንም ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በሀገር ውስጥ ለሚሰሩ አዳዲስ(ኢኖቬቲ) ፈጠራዎች ትኩረት በመስጠት በራስ ነባራዊ ሁኔታ በመቀየር ቴክኖሎጂዎችን ማሻሻል የሚቻልበት መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል። መንግሥት ከላይ ወደታች የሚሄድ አሠራር በመተው በተለይ ለባለሙያው ትኩረት ሰጥቶ በእያንዳንዱ ነገር ላይ ባለሙያውን በማሳተፍ የመረጃ እና እውቀት ክፍተት እንዳይፈጠር ማድረግ ይገባል ይላሉ፡፡

አቶ ጥላሁንም ህብረተሰቡ ላይ በመስራት አስፈላጊነት ላይ የሰጡት ሀሳብ የአቶ ፊሊክስን ሀሳብ ያጠናክራል። አሁን ያለንበት የመረጃ ጊዜ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፣ በመረጃ የበለጸገ ህብረተሰብ መገንባት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ፤ ቴክኖሎጂ ማምጣት ላይ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ ላይ መሥራት እንደሚገባም ነው ያሳሰቡት። ‹‹በመረጃ የበለጸገ በእውቀት የሚመራ ህብረተሰብ ማምጣት ከቻልን ህብረተሰቡ ራሱ ኢንተርኔትን ይጠይቃል፤ ቴክኖሎጂን ይፈጥራል›› ሲሉ ያስረዳሉ።

አቶ ጥላሁን እንደሚሉት፤ ህብረተሰቡ ዘንድ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በደንብ የማስተዋወቅ እንዲሁም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በደንብ መሰራት ይኖርበታል። የኢንፎርሜሽን ኢንዱስትሪው ጥቅም እንዳለው፣ ሕይወትን መቀየር እንደሚችል ማስገንዘብና ማሳወቅ ይገባል ይላሉ። ‹‹ሰው በልቶ ማደር እንዲችል ለማድረግ በምንሰራው መጠን በእውቀት የታነጸ ህብረተሰብ ሲኖር ደግሞ በራሱ እውቀት መብላት እንዲችል መረጃዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልገው ማስተማር ያስፈልጋል›› ባይ ናቸው ፡፡

የዓለም ሀገራት ከኛ ተሽለው የተገኙት የራሳቸውን እሴት ይዘው በመገኘታቸው ነው የሚሉት አቶ ጥላሁን፤ ቴክኖሎጂዎች ስናላምድ ከቴክኖሎጂው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ነገሮች ላይ እምብዛም አልተሰራም ሲሉም ይጠቁማሉ። እንደ ጃፓን፣ ቻይና የመሳሰሉት ሌሎች ሀገሮችን የቴክኖሎጂ እድገታቸውን ብንመለከት መጀመሪያ ከራሳቸው ውስጣዊ ችግር ተነስተው ነው ምርምሮችንም ሆነ የፈጠራ ሥራዎችን የሚሰሩት የሚሉት አቶ ጥላሁን፤ እኛ ግን ያለብን ችግር በጥልቀት አንለይም እንዲሁም አናጠናም ይላሉ። ‹‹ችግራችንን የምንፈታው እነሱ የሰሩት ቴክኖሎጂ በቀጥታ ወስደን በመጠቀም ነው፤ የወደፊት መፍትሔ ሊሆን የሚገባው ችግሮቻችን በራሳችንን መፍታት የሚያስችሉ ሀገር በቀል እውቀቶችን በማስፋፋት መጠቀም ስንችል ነው ብለዋል።

አሁን ኢንተርኔት ኖሮ እኮ ተደራሽ የምናደርገውና የምናገራው እንዲሁም የምንጫወትበት የመረጃ አካባቢ ሌሎች ሀገራት በሰሩት ፕላት ፎርም ላይ መሆኑን ነው ሲሉ አቶ ጥላሁን ይናገራሉ። በምንፈልገው መጠንና ልክ ኢንተርኔት ቢኖረን እንኳን፣ የትኛውን የራሳችንን ዳታ ነው ተደራሽ የምናደርገው? በየትኛው ዳታ ነው ኢንተርኔትን ተጠቅመን ለችግራችን መፍትሔ የምንፈልገው የሚለው ከወዲሁ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው ይላሉ። ስለዚህ መጀመሪያ የራሳችን የምንለውን ነገር በደንብ መገንባት፣ ከዚያ ባሻገር ደግሞ የአስተዳደሩን ሥራ መሥራት፣ ሰዎች በኢንተርኔቱ ዘርፍ ያላቸውን እውቀት በደንብ ማሳደግ ቀጣዩ ትልቁ ሥራችን መሆን አለበት ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ በቅርቡ በተካሄደው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፤ ኢትዮጵያ በዲጂታል ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ ፈጣን ለውጥ እያመጣች መሆኑን ጠቅሰው፤ የበይነ መረብ አገልግሎት የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተያዘውን የአሥር ዓመት እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ፋይዳ እንዳለው አስታውቀዋል።

‹‹በዘመነ ዲጅታል የበይነ መረብ ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በትራንስፖርት፣ በግብርና እንዲሁም በጤና እድገት ላይ ዘርፉ ያለውን አወንታዊ ድጋፍም አመላክተዋል። ኢትዮጵያ በኮቪድና በሌሎች ሰው ሠራሽ ችግሮች በተፈተነችበት ወቅት ሥራን በበይነ መረብ ማካሄድ መቻሏን አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲበረታቱ ማድረጉንም በመልካም ጎኑ ማንሳታቸው ይታወሳል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ወደ አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚ በምታደርገው ጉዞ አንድ ወጥ የሆነ ራዕይ ያስቀመጠ ብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ በሥራ ላይ ማዋሏን የጠቆሙት ዶክተር ዐቢይ፣ ስትራቴጂው መሠረተ ልማትን ማጎልበት፣ ሥርዓቶችን ማስቻል፣ ዲጂታል መድረኮችን እና የዲጂታል ሥነ-ምሕዳርን በመገንባት ላይ ያተኩራል ማለታቸውም ይታወቃል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በቅርቡ በአዲስ አበባ በተካሄደው 17ኛው የዓለም የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ላይ ብዙም ባስተላለፉት መልእክት በዓለም አቀፍ ደረጃ በበይነ መረብ ተደራሽነት ላይ በስፋት መስራት እንደሚያስፈልግ መጠቆማቸው ይታወቃል። አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት እንደሚያስፈልግም ማስገንዘባቸው ይታወሳል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት እስከ ምን ድረስ?

**አስመረት ብስራት**



ምንም አይነት አስተሳሰብ ያለው ግለሰብ ወይም ቡድን የፖለቲካ ፍላጎት ቢኖረውም ባይኖረውም የተለያዩ አይነት የመገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በሚያሰራጫቸው ሀሰተኛና የተዛቡ መረጃዎች ሳቢያ በሚፈጠሩ አለመረጋጋቶች እና ግጭቶች በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዋነኛ ሰለባዎቹ ንጹሐን ዜጎች ናቸው፡፡

ሀሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ዜጎችን ማታለል፣ ማደናገርና ለጉዳት ማጋለጥ፣ የህብረተሰቡን የአንድነት፣ የወንድማማችነትና የመቻቻል ባህልን ማዳከም፣ የብሔርና የሃይማኖት ግጭቶች እንዲፈጠሩ ፅንፈኛ አጀንዳዎችን ማቀንቀን ማህበረሰብ ይቅር የማይለው ወንጀል እንጂ በየትኛውም መመዘኛ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ተደርጎ ሊታሰብ አይችልም፡፡

የተዛባ እና ሀሰተኛ መረጃ ማሰራጨት ሕዝብን እርስ በእርስ ማጋጨት ወይም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል አለመግባባትን እንዲፈጠር ማድረግ ሀገር ወዳድነትን ወይም ለሕዝብ ጥቅም መስራት ሊሆን እንደማይችል ግልፅ ነው። ለየትኛውም የኀብረተሰብ ክፍል ለግጭት ማነሳሳት የጥፋት እንጂ የመፍትሄ መንገድ አይሆንም።

በመሆኑም ሀሰተኛና የተዛባ መረጃ የሚያሰራጩ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማድረግ በዜጎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የመከላከልና ሀገርን መታደግ ከመሆኑ ባሻገር የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከሚደረጉት እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱ መንግሥታዊ ግዴታና ተግባር ነው፡፡

ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ሽፋን አድርገው ሀሰተኛ መረጃዎችን በማሰራጨት ሕዝብን የሚያደናግሩና የተለየ ዓላማ ለማሳካት ታች ላይ የሚሉ ሀሰተኞችን አደብ ለማስያዝ እንደ ሕዝብ ውሸትን ያለማዳመጥ መፍትሄ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

አንድ ሃይማኖት በሌላ ሃይማኖት ላይ እንዲነሳ፤ በብሔርና ብሔር መካከል ግጭት በመፍጠር የማህበረሰብን አብሮነት የሚያጠለሹ የጥላቻ ንግግሮችን የሚናገሩ፤ በተዛባ መረጃ ሕዝብን በሕዝብ ላይ የሚያስነሱ፤ መንግስትና ሕዝብ እንዳይተማመኑ የሚያደርጉትስ የመናገር ነፃነታቸውን ተጠቀመው ነው? የመናገር እና የሚዲያ ነፃነትስ እስከምን ድረስ ነው? ስንል የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነፃነት ዳይሬክተር አቶ ማናዬ አለሙን፤ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያ አቶ ሰለሞን ጎሹን እና የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር ፍሬዘር እጅጉን አነጋግረናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነፃነት ዳይሬክተር አቶ ማናዬ አለሙ በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት መሰረቱ ህገ መንግስቱ ነው ይላሉ። የህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ማንኛውም ሰው የፈለገውን ሀሳብ የማዳመጥ፤ የፈለገውን ሀሳብ የመያዝ፤ የፈለገውን ሀሳብ የማስተላለፈ መብቱ በህገ መንግስቱ ተቀምጧል። በዛው ልክ መብቱ ፍፁም መብት ተደርጎ ያልተቀመጠ ሲሆን ሁልጊዜ ከመብቱ እኩል ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች ይኖራሉ። ታሳቢ ከሚደረጉ ጉዳዮች ውስጥ የሕዝብ መብት፤ የወጣቶች ደህንነት፤ የሀገር ደህንነት፤ የግለሰቦች ክብር ወይም ግላዊነትን ታሳቢ በማድረግ ገደቦች ይጣላሉ።

ማንኛውም ሰው ሀሳቡን መግለፅ ይችላል ሲባል እንደፈለገ ያወራል ማለት አይደለም፡፡ በህግ አግባብ የተጣሉ ገደቦችን ጠብቆ በዛ መልኩ የሚናገረውን ሀሳብ የሚገልፅበት ስርዓት ነው። በህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ ገደቦቹ በግልፅ ተቀምጠዋል። የወጣቶችን ደህንነት የሚነካ፤ መልካም አስተዳደር ላይ ተጽእኖ የሚፈጠር፤ የሀገር ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል፤ የግለሰቦችን ክብር በሚነካ መልኩ ማንቋሸሽ አይቻልም የሚሉ ገደቦች ተቀምጧል። በእነዚህም መሰረት የሀሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግርን ለመከላከል አዋጅ ቁጥር 11/85 ታውጇል፡፡

ማንነትን፤ ብሔርን፤ ቋንቋን መሰረት አድርጎ በሌሎች ዘንድ በጥላቻና በጥርጣሬ እንዲታይ ማድረግ ወንጀል መሆኑን ያመለክታል። ሌላው ሀሰተኛ መረጃን ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ሶስተኛ ወገንን ለመጉዳት በማሰብ ሀሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ላይ መገኘት ወንጀል ነው። ለዚህም ለማስተማርና ፍትህ ለማሰጠትም የተለያዩ ተቋማት ሀላፊነቱን ወስደዋል ይላሉ።

**ሀሳብን የመግለፅ መብት ሰብዓዊ መብት ከመሆኑ አንፃር ገደብ ሲጣልበት ባይገባም ለሀገር ደህንነት ለሕዝብ ሰላም ሲባል በህገ መንግስት ላይ ገደብ ሲጣልበት እንደሚችልም ተቀምጧል**

የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያ አቶ ሰለሞን ጎሹ በበኩላቸው ማንኛውም ሰው ሰው በመሆኑ የተሰጠው መሰረታዊ መብት አለው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ግዴታ አለበት። ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት የግለሰቦች ነፃነት ይሆንና በተቋማዊ አደረጃጀታቸው በተቋማዊ ይዞታቸው የመገናኛ ብዙሃን ደግሞ ተቋማዊ የሆነውን ነፃነታቸውን የሚመለከት ነው። እንደ ሰው እንደ ጋዜጠኛ ሲሰራ በግለሰብ ደረጃ የሚሰጠው ሀሳብን የመግለፅ መብት በጣም ሰፊ ሲሆን፤ የፕሬስ ነፃነት ግን ፕሬስ ባለው ተቋማዊ ይዘቱ መሰረት ጥበቃ አለው። ይህም ከህገ መንግስቱ ጀምሮ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ስምምነቶችና የተለያዩ የህግ ማእቀፎች የሰጣቸው ነፃነቶች ላይ የተቀመጠ ነው።

ግለሰቦች ሀሳብን በነጻነት የመግለፅ መብታቸውን በሙሉ እንዲጠቀሙ የተቋማት አደረጃጀት ያስፈልጋል። አንድ መረጃ ለሁሉም እንዲዳረስ መገናኛ ብዙሃን ያስፈልጋሉ። ይህ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ብዙሃኑ ጋር እንደመድረሳቸው ገደብ ቢኖራቸውም፤ ለፕሬስ ነፃነት ሰፊ የሆነ ጥበቃና ሰፊ የሆነ መብት እንዲሰጠው ሆኗል።

መገናኛ ብዙሃን ነፃ በመሆናቸው የተነሳ መረጃዎችን የመቀበል፣ መረጃዎችን የማድረስ፣ ሀሳብን ለሌሎች የመካፈል ደግሞም ከሌሎች የመቀበል መብት እና ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ሂደት ሀሳብን መያዝ መቀበልና ማስተላለፍ በተቋማዊ ቅርፁ ጥበቃ እየተደረገለት የሚሰራ ሲሆን የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ይባላል።

የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት ቢኖራቸውም ነፃነታቸው እስከምን ደረስ ነው? ሲባል መገናኛ ብዙሃን ገደብ አለባቸው። ከላይ እንዳልነው ከተቋማዊ ጥበቃ አንፃር የተሻሉ ጥበቃዎች ሊሰጣቸው ይችላል እንጂ፤ ሀሳብን በነፃነት መስጠት በራሱ ገደብ አለው።

ገደቦቹም በዓለም አቀፍ ህግ መሰረትም ሆነ ኢትዮጵያ እነዛን የዓለም አቀፍ ህጎች ተቀብላ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 6 ላይ ምን ሲሆን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ገደብ ይኖረዋል? የሚለውን ለመመልከት ከሌሎች ተነፃፃሪ መብቶች አንፃር ጉዳዩ ይመረመራል። ለነፃነትም ገደብ ሲቀመጥ እንዲሁ አይደለም፡፡ ማንም ዝም ብሎ ገደብ ሊያበጅለት አይችልም። ህግ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው አግባብነት ያለው ኃይል በሚያወጣቸው ህጎች አማካኝነት ገደብ ሊደረግ ይችላል። ሁለተኛው እነዛ ገደቦች የሚደረጉት ከተነፃፃሪ መብት ጋር ታይተው ነው።

እዚህ ላይ መብቱ የሚገደበው የሌላውን መብት ለመጠበቅ ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ ገደቡን የወቅቱ መንግስት ወይም ጉዳዩን ተፈፃሚ የሚያደርገው አካል ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፡፡ እዚህ ላይ በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው መስፈርት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በመስፈርትነት የተቀመጡ ገደቦች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በሀገራችን የህግ አግባብ የወጣቶችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል፤ የጦርነት ፕሮፖጋንዳን ለመጠበቅ ሲባል እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ ገደብ ይደረጋል ይላሉ።

የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት ትምህርት ክፍል መምህር ፍሬዘር እጅጉ በበኩላቸው በሀገራችን የመረጃ ነፃነትንም ሆነ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚጠብቅ አዋጅ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ላይ ተቀምጧል። እዚህ አንቀፅ ላይ ዋናው መሰረታዊ ነገር አንድ ግለሰብ ሀሳቡን በማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ተጠቅሞ ሀሳቡን መግለፅ መብቱ እንደሆነ ተቀምጧል። መገናኛ ብዙሃንም እንደተቋም ሀሳብን የማንሸራሸር መብታቸው በግልፅ ተቀምጧል።

ሀሳብን የመግለፅ መብት ሰብዓዊ መብት ከመሆኑ አንፃር ገደብ ሊጣልበት ባይገባም ለሀገር ደህንነት ለሕዝብ ሰላም ሲባል በህገ መንግስት ላይ ገደብ ሊጣልበት እንደሚችልም ተቀምጧል። ሀሳብን የመግለፅ መብት ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል መቀመጡን ተከትሎ በተለያዩ ጊዜያት በሀገሪቱ የወጡ አዋጆች ላይ የተለያዩ ገደቦች ሰፍረዋል። ለአብነት ያህል የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል በወጣው አዋጅ 1185/2012 ላይ በግልፅ አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን በብሔሩ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳኝነት ወይም በመገለጫዎቹ ጥላቻን የሚቀሰቅሱ መድሎን ሊያመጡ የሚችሉ ንግግሮች ገደብ የተጣለባቸው ናቸው፡፡ ይህንን ጉዳት ሲፈፅሙ የተገኙ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ቅጣት ተጥሎባቸዋል።

ሀገሪቱ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን ለማስተዳደርና ለመምራት የተቋቋመ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የተባለ ተቋም አለ። ይህ ባለስልጣን በሀገሪቱ ያሉ መገናኛ ብዙሃን በተሻለ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ መደላድል የሚፈጥር እንዲሁም በህግ የተቀመጡ ጉዳዮችን አልፈው ሲገኙ የተለያዩ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንደሚወስድ በአዋጁ ስልጣን ተሰጥቶታል።

ሀገሪቱ በጦርነት ወቅት በነበረችበት ጊዜ የህግ ማእቀፍ ተጥሷል ተብሎ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሲወሰድባቸው የታየ ሲሆን፤ በቅርብ ጊዜ ግን የጥላቻ ንግግርን በመናገር ሕዝብን በማነሳሳት የተጠየቁ አካላት እንዲህ ነው የሚባሉ እርምጃዎች ሲወሰድባቸው አይታይም።

ይህ ግን ሀሰተኛ መረጃም ሆነ የጥላቻ ንግግርን በመደበኛ መገናኛ ብዙሃንም ሆነ በማህበራዊ ድህረ ገጾች የሚነገሩ የጥላቻ ንግግሮች እንዳሉ እየታወቀ፤ ተጠያቂነት ኖሮ ቅጣት ተሰጥቷቸው ሌሎች ትምህርት እንዲወስዱ ሲደረግ አለመታየቱ ጉዳዩ እንዳይቀንስ ያደረገው ይመስለኛል።

ለዚህ ችግር መፍትሄ ይሆናል ያሉትን አቶ ማናዬ አለሙ ሲጠቅሱ፤ ሀገሪቱ ውስጥ ለበርካታ ጊዜያት በሬ ወለደ አይነት ዜናዎችን መስማት የጥላቻ ንግግሮችን ማየት የተለመደ ነው። ለዚህም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃኑ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። ዋናዎቹ ሚዲያዎችም ግን ከዚህ የፀዱ አለመሆናቸው ይታያል።

ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃንን የተጠያቂነት ሁኔታ እጅግ አናሳ ነው። የት እንዳሉ አይታወቅም፤ ስለዚህም ማህበራዊ ሚዲያውን የማዘጋት ስራ የተሻለ አማራጭ በመሆኑ መንግስት ከልክ በላይ ማህበራዊ ሚዲያዎችን የማዘጋት ስራ ይሰራል። ከዚህ ይልቅ ዋናዎች መገናኛ ብዙሃን ከእነዚህ ተግባራት የፀዱ እንዲሆኑ ማድረግ፤ መንግስት ለመረጃ ክፍት በመሆን የሚፈበረኩ ሀሰተኛ ዜናዎች እንዳይኖሩ ማስቻል ጉዳዩን ቀላል ያደርገዋል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል።

አዋጁም ተጠያቂነቱም በግልፅ ተቀምጦ ሲፈለግ ተግባራዊ የሚደረግ ሳይፈልግ የሚተው መሆን አይገባውም፤ በወጥነት ማስተማሪያ የሚሆን ቅጣት መተላለፍ አለበት። በተጨማሪ የማይፈፀም ህግ መውጣት የለበትም አዋጁ በአላማ በመውጣቱ አላማውን ማስፈፀም የግድ ነው። ይህም መንግስት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው ብለዋል።

አቶ ሰለሞን ጎሹ በበኩላቸው፤ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ገደቦች እንዳይጣሱ፤ የጥላቻ ንግግሮች እንዳይሰራጩ ለሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ለኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የቅድመ መከላከል ሀላፊነት ተሰጥቷል። የጥላቻ ንግግርን ከስሩ ለማድረቅ ለእነዚህ ሁለት ተቋማት የማስተማር ስራ እንዲሰራ ተደርጓል። አቃቤ ህግ ደግሞ ማንኛውንም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ጉዳዮችን ይከታተላል፤ ማንንም ሳያስፈቅድ ይከሳል። ፍትህ ሚኒስቴርም የመጨረሻ ውሳኔውን የሚያደርግ አካል ነው። ስለዚህ ተጠያቂነቱ እንዳለ ሆኖ የመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ይህንን አድርገው የተገኙ ሰዎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወሰድባቸዋል።

መፍትሄው ጉዳዩ የመብት ጉዳይ እንደመሆኑ ተጠያቂነትን ለማንሳት ገደቦቹ እስከምን ድረስ እንደሆኑ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ቅጣት ቢኖርም ቅጣት የተሰጠበትን አግባብ ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

መምህር ፍሬዘር እጅጉ የመገናኛ ብዙሃን በአጠቃላይ ከተለያየ ተፅእኖ ራሳቸውን ገለልተኛ አድርገው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል። መገናኛ ብዙሃን ተቋማዊ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሃይማኖት መገናኛ ብዙሃን በልዩ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ተደርጓል። እነዚህ ተቋማት አሰራራቸው በምን መልኩ እንደሚቃኝ ባይታወቅም፤ በአዋጁ ላይ የተቀመጠው ግን ማንኛውም ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራም በሃይማኖቶች መካከል ግጭት ማነሳሳት የሌሎችን ሃይማኖቶች ወይም እምነት ማንኳሰስ በሌሎች ሃይማኖቶች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር ማድረግ የለበትም።

ይህን ገደብ በመከተል የሃይማኖቶች ልዩነት ላይ ግጭት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል። ህግ ላይም በተቀመጠው ልክ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በመፍጠር ሃይማኖታዊ መገናኛ ብዙሃን በህግና በስርዓት እንዲመሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

ሌላው መፍትሄ ማህበረሰቡ የመገናኛ ብዙሃን እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህ ማለት በማንኛውም መገናኛ ብዙሃን የተላለፉ መረጃዎችን በተለያዩ መመዘኛዎች ውስጥ ከቶ ማህበረሰቡ በተገቢው መልኩ በግንዛቤ በመመራት ከግጭት የፀዳ ማህበረሰብ እንዲኖር መደረግ አለበት።

ይህም ህፃናት ከልጅነታቸው ጀምሮ የመገናኛ ብዙሃን እውቀት ኖሯቸው፤ በእውቀት የተመራ ማህበረሰብ መረጃን መዝኖ አንጥሮ እንዲቀበልና እንደ ማህበረሰብ እሴቱን ጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ ተገቢ ነው ሲሉ የመፍትሄ ሀሳብ ያሉትን አጋርተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የወሊድ ፈቃድ ዘመቻ መስራቿ

**ሰላማዊት ውቤ**

“ባለ ትዳርና የመንግስት ሠራተኛ ነኝ። ልጅ የወለድኩት የመውለጃ ጊዜዬ ሊያልፍ በተቃረበበት ወቅት ነው። ሰው ባይረዳኝም ዘግይቼ የወለድኩበት የራሴ ምክንያት ነበረኝ” ሲሉ የእናትነት ተሞክሯቸውን ያካፈሉን ወይዘሮ ሣራ ገብረማርያም ናቸው። ወይዘሮዋ እንደሚናገሩት ዘግይተው የወለዱበት ምክንያት ብዙ ነው። በወቅቱ የወሊድ ፈቃድ በቂ የነበረ አለመሆኑ የመጀመሪያው ሲሆን ከ40 ባልበለጠ ቀናት ውስጥ ዘጠኝ ወር ሙሉ ተሸክመውት የቆዩትንና በጭንቅ ምጥ የተገላገሉትን ጨቅላ ህፃን ልጃቸውን ጥለው ወደ ሥራ ለመመለስ ይገደዱ ነበር።

በዚህ የወሊድ ጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሥራ ገበታቸው የተመለሱ ብዙ እናቶች እንዳጋጠሙዋቸው ወይዘሮ ሣራ ይናገራሉ። የጡታቸው ወተት እየፈሰሰ ሲቸገሩ የነበሩ እናቶችም በተደጋጋሚ አጋጥመዋቸዋል። እናቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ስለሚገደዱም ህጻናቱን ለሰራተኞች ለመተው ይገደዳሉ። ህፃኑን የተውላቸው ሠራተኞችም ይሁኑ ቤተሰቦች እንደራሳቸው የእናትነት ፍቅር እየሰጡ ሊንከባከቡና ሊጠብቋቸው ባለመቻላቸው ቅሬታ ሲሰማቸው ታዝበዋል።

በተለይ ህፃን ልጆቻቸውን ለሰራተኛ ትተው ወደ ሥራ ገበታቸው የተመለሱ እናቶች ልጆቻቸው በመውደቅና በተለያየ ምክንያት ለጉዳት መዳረጋቸውን በፀፀት ሲናገሩ አድምጠዋል። ጓደኛቸው “ልጄን የአእምሮ ዝግመት የያዘው ሰራተኛዬ በሁለት ወሩ ጥላብኝ ነው” ስትል የነገረቻቸውን ለአብነት ያነሳሉ። እሳቸው ሳይወልዱ የዘገዩበት ምክንያት ይሄን ዓይነቱን ችግር ከመፍራት የዘለለ አልነበረም። ከወለዱ ጀምሮ ቢያንስ እስከ ስድስት ወር ድረስ ለልጃቸው ጡታቸውን ከማጥባት ጋር የእናትነት ፍቅር በመስጠት መንከባከብ መፈለጋቸው ሌላው ምክንያታቸው ነበር። 40 ቀን የወሊድ ፈቃዳቸው ሲያልቅ ያልጠነከረ ልጃቸውን ጨክነው ጥለው ወደ ሥራ ለመመለስ የሚደፍር አንጀት ያላቸው ባለመሆኑ ለመውለድ ዘግይተዋል።

ሌላዋ የወሊድ ፈቃድ ተሞክሮዋን ያካፈለችን የ24 ዓመቷ ወጣት እናት ስንዱ አየነው ትባላለች። ስንዱ እንደነገረችን የመጀመሪያ ልጇን የወለደቻት የዛሬ ሰባት ዓመት ነው። ያኔ ትሰራ የነበረው በአንድ የግል ድርጅት ነበር። የድርጅቱ ባለቤት ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ይፈልግና በስልክም ይጨቀጭቃት ስለነበረ 40ውን ቀንም በመከራ ነው የቆየችው። በዚህ ላይ እሷ ወደ ሥራ ስትመለስ ልጇን የሚይዝላት ሰው አልነበራትም ። ወላጅ አልባ በመሆኗና እኳለ ማውታ በማደጓ ዘመድ አልነበራትም። ልጇን የሚጠብቅላት ሰራተኛ እንዳትቀጥር ደሞዟ ለቀለቧና ለልጇ ሳሙናም አይበቃም።

አጋጣሚ ሆኖ ልክ ወደ ሥራ መመለሻዋ ዕለት ልጇ ክፉኛ ታመመ። ሆስፒታል ይዛው ሄደች። ስላልተሻለው በማግስቱ ቀረች። በሦስተኛው ቀን ልጄ ስለታመመብኝ ፈቃድ ይሰጠኝ ብላ ወደ ሥራ ቦታዋ ስትሄድ በእሷ ቦታ ሌላ ሰው ተተክቶ አገኘች። ምነው ወደ ሥራዬ መልሱኝ ብትል አሰሪዋ የተሰጠሽን ፈቃድ እንደጨረሽ ሥራ ገበታሽ ላይ ባለመገኘትሽ ሌላ ሰው ስለቀጠርን ልንመልስሽ አንችልም አላት።

ጋዜጠኛና ደራሲ ሮዝ መስቲካ የነዚህን ተሞክሯቸውን ያካፈሉንንና የሌሎቹን ወላድ ሠራተኛ እናቶች ጽዋ በመጠኑም ቢሆን ቀምሳ አይታዋለች። ሮዝ ሦስተኛ ልጇን ወልዳ እያጠባች ባለችበት ወቅት የቀመሰችው ጽዋ ከብዙ ወላድ እናቶች ገጠመኝ ጋር በአእምሮዋ ሲብሰለሰል በመቆየቱ እረፍት አሳጣት። ሠራተኛ እናቶች በሚወልዱበት ወቅት የሚሰጣቸው የወሊድ ፈቃድ ጨቅላ ልጆቻቸውን በተገቢ ሁኔታ እንዲንከባከቡና እንዲያጠቡ የሚያስችል አለመሆኑን እንደ ሌሎቹ የጾታ አጋሮቿ በዝምታ ልታልፈው አልወደደችም። ሮዝ ዕድለኛ ሆና አማራጭ ስላላት ከአንዱ ሥራ ወደ ሌላው ሥራ ልትዛወር ብትችልም ይሄን ማድረግ ያስገደዳት ሁኔታ የተሰጣት የወሊድ ፈቃድ በማነሱ መሆኑ የሌሎች ሴቶች ችግር የበለጠ እንዲሰማት አደረጋት። ሁኔታቸው ከራሷ ጋር ተዳምሮ መላ እንድትላቸው ቆሰቆሳት።

እናም ሮዝ መስቲካ ፈጥና ይሄን ድምፅ ለማሰማት



ሮዝ መስቲካ

**በተለይ ህፃን ልጆቻቸውን ለሰራተኛ ትተው ወደ ሥራ ገበታቸው የተመለሱ እናቶች ልጆቻቸው በመውደቅና በተለያየ ምክንያት ለጉዳት መዳረጋቸውን በፀፀት ሲናገሩ አድምጠዋል። ጓደኛቸው “ልጄን የአእምሮ ዝግመት የያዘው ሰራተኛዬ በሁለት ወሩ ጥላብኝ ነው” ስትል የነገረቻቸውን ለአብነት ያነሳሉ**

ሦስተኛ ልጇን እያጠባች የወሊድ ፈቃድ ዘመቻን መሰረተች። የወሊድ ፈቃድ ስድስት ወር እንዲሆን የሚጠይቀውን ዘመቻ የጀመረችው በኦንላይ ሲሆን የወሊድ ፈቃዱ አሁን ላይ በቂ ባለመሆኑ ይጨመር የሚሉ ተከታዮቿ ቁጥር ከ10ሺህ በላይ ደርሷል።

‹‹ህፃናት የጨቅላነት ጊዜያቸውን ጨምሮ እስከ ስድስት ወራቸው በእናታቸው ጉያ ውስጥ ሆነው ነው ማሳለፍ ያለባቸው›› የምትለው ሮዝ ብዙ ሰራተኛ እናቶች ይሄን ዕድል ባለማግኘታቸው የተሰጠቻቸውን አጭር የወሊድ ፈቃድ ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ለመመለስ ሲቸገሩ የነበረበት ሁኔታ መኖሩን ታስታውሳለች። የወሊድ ፈቃዱ አጭር በመሆኑ ልጆቻቸውን የእናትነት ፍቅር እያጋሩ መቆየት ቀርቶ ጡት ማጥባት እንኳን አለመቻል፣ ወደ ሥራ በሚመለሱበት ወቅት ልጆቻቸውን የሚይዝላቸው ሰው ማጣት፣ ሰራተኛ የመቅጠር አቅም ማነስ፣ ሰራተኛ የመቅጠር አቅም ያላቸው ቢኖሩም አንዳንድ ሠራተኞች ለልጅ አያያዝ የሚመቹ አለመሆናቸውና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

ከዚህ አኳያም ብዙ እናቶች ልጆቻቸውን ለሰው አሲዘው ወደ ሥራ ለመመለስ ደስተኛ ያለመሆናቸው ከችግሮቹ እንደሚጠቀሱ ታስምርበታለች። እናቶች ወደ ሥራ ሲመለሱ ለሰራተኞች የሰጧቸው ህፃናት ልጆቻቸው የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። የከፋ የስነ ልቦና ችግርም ይገጥማቸዋል። ጉዳቱ የቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ይተርፋል። ያኔ የወሊድ ፈቃድ እንደ ዛሬው አራት ወር ቢሆንና እሷም በወለደችበት ወቅት ይሄን ያህል በተለይም ልጇን ምግብ ማስጀመር እስከምትችልበት ስድስት ወር ቤቷ ውስጥ ከልጇ ጋር ቆይታ ቢሆን፣ እንዲሁም የህፃናት ማቆያ በየመሥሪያ ቤቱ ቢኖር ወደ ሥራዋ ገብታ ተመልሳ ለመሥሪያ ቤቷ አስተዋጽኦ ታደርግ እንደነበር ታነሳለች። ለራሷም የገንዘብ አቅሟን ታሳድጋለች። የወሊድ ፈቃድ በቂ ባለመሆኑና የህፃናት ማቆያ በየመሥሪያ ቤቱ ባለመኖሩ ኑሮ የከበዳቸው ወላድ እናቶች አማራጭ ስለሌላቸው ልጆቻቸው ላይ ጨክነው ወደ ሥራቸው ይመለሳሉ። የባሰባቸው እናቶች ደግሞ ስራቸውን በመልቀቅ እቤታቸው ቁጭ ብለው ልጆቻቸውን ማሳደግ ይመርጣሉ።

ሮዝ እንደምትናገረው የስድስት ወር የወሊድ ፈቃድ ዘመቻውን የጀመረችው ይሄን ሁሉ ታሳቢ አድርጋ ነበር። በእርግጥ ጥረቷ ውጤት አፍርቶ 40 ቀናት የነበረው የወሊድ ፍቃድ ወደ አራት ወራት እንዲያድግ በመንግስት ተወስኗል። ያኔ ታዲያ ብዙ ደጋፊዎች የማግኘቷን ያህል ሴቶችን ስራ ፈት፣ ሀገሪቱን ደግሞ ደሃ ለማድረግ ነው በማለት ዘመቻዋን የተቃወሟት አሉ። ‹‹አንቺ ይሄን እንዴት ልታስቢ ቻልሽ›› ያሏትም ነበሩ። የዘመቻው መስራች ጋዜጠኛ እንደመሆኗ የወሊድ ፈቃዱ በቂ ባለመሆኑ እሷንና ሌሎች ሰራተኞችን በተጨባጭ የገጠማቸውን ከማስረዳት በዘለለ የሴቶች ጉዳይ የሀገር ጉዳይ መሆኑን በማንሳት ስትሞግት ቆይታለች።

ምክንያቱም እናት በምትወልደው ልጅ ሀገር እየገነባች ትውልድ እየቀረጸች ነው። እንዲያውም ባለፉት ሦስት ዓመታት በተለያየ መልኩ በሀገሪቱ ላይ የተከሰተው የእርስ በእርስ ግጭትና መናቆር፣ በዚሁ ምክንያት የጠፋው የሰው ሕይወትና የወደመው ንብረት መንስኤው የቢሮ ሠራተኛ እናቶች በቂ የወሊድ ፈቃድ አግኝተው ልጆቻቸውን በመልካም ስብዕና ማሳደግ ባለመቻላቸው የተነሳ መሆኑን ጋዜጠኛ ሮዝ ትሞግታለች። በዋነኛነት እናቶች በቂ ፈቃድ ሳያገኙ ወደ ስራቸው በመመለሳቸው ለህፃናት ጤናማ ዕድገት ወሳኝና መሰረታዊ የሆነውን ተፈጥሯዊውን የጡት ማጥባት ሂደት ማሳካት አለመቻላቸውን በማንሳት የዘመቻውን መነሻ ትጠቅሳለች።

ሮዝ የወሊድ ፈቃድ እንዲራዘምና እናቶች በበቂ ሁኔታ ልጆቻቸውን ማሳደግ እንዲችሉ የጀመረችው ዘመቻ ተቀባይነት አግኝቶ መንግስት የወሊድ ፈቃድን ለመንግስት፣ ለግል ሰራተኞች እያለ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ወደ አራት ወር ሊያደርሰው በቃ። በሚገርም ሁኔታም እነ ሮዝን ፈትኗቸው የነበረውን ችግር በየፈርጁ ለመፍታት በየተቋማቱ የህፃናት ማቆያዎች በስፋት ማቋቋም ጀመረ። በየጤና ተቋማቱም የእናት ጡት ለነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናት ጤናማ ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ ከመስበክና እናቶች ልጆቻቸውን እንዲያጠቡ ከማበረታታት ጀምሮ ብዙ ዘመቻውን የሚያጎሉ እርምጃዎችን ወሰደ።

እቤቷ ሆና ሦስተኛ ልጇን እያጠባች በዚህ መልኩ ስኬት ያገኘውን የወሊድ ፈቃድ የጀመረችው ሮዝ በኑሯቸው ምክንያት ከሥራቸው መቅረት ለማይችሉ ሴቶች፣ እንዲሁም የነገ ሀገር ተረካቢ ለሆኑ ህፃናት መልካም ዕድገት የምታደርገውን ጥረት በዘመቻው ብቻ አልገታችውም። ጨቅላ ልጄን ጨክኜ ጥዬ ወደ ሥራ ገበታዬ አልመለስም በማለት ጨቅላ ልጇን በጡቷ ተንከባክባ እያሳደገች ሁለት መጽሐፍት ከመፃፍ ባሻገር የዛሬ አምስት ዓመት ምቾት የተሰኘውንና አሁን ላይ ወደ ምቾት መልቲ ሚዲያ ወደ መሰኘት የሰፋውን የሬዲዮ ፕሮግራም አቋቋመች። መሰረቱን እናት በምትጥለው ቤተሰብ ዙሪያ በማድረግ ሰርከ ቅዳሜ ግንዛቤ ማስጨበጡን ተያያዘችው። በፕሮግራሙ ስለ እናት ጡት ጠቀሜታ በሰፊው ይወራበታል። እናቶች ከወሊድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ህጎች፣ ፖሊሲዎችና ሌሎች ከመብቶቻቸው ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ሲያነሱ ምላሽ ይሰጥባቸዋል። አቅጣጫ ይመለከትባቸዋል። መፍትሄም ይጠቆምባቸዋል።

ከገንዘብ በላይ ስለሆነው እናትነት ‹‹እኛ እናቶች ጡረታችንን እያሰብን ነው። ለጡረታችን እየሰራን ነው ብዬ ነው የማስበው›› የምትለው ሮዝ የዛሬ ሦስት ዓመት አራተኛ ልጇ ወደ ህፃናት ማቆያ ስትገባ እሷ ወደ ሥራዋ መመለሷንም አውግታናለች። ሮዝ ለቤተሰብ ብሎም ለሀገር ግንባታ መሰረት በሆኑት እናቶች ጉዳይ ዛሬም ያገባኛል ብላ ከመሥራት አልተቆጠበችም። አሁን ላይም መንግስት የወሊድን ፈቃድ ከአራት ወደ ስድስት ወር እንዲያሳድግና የመንግስት ሰራተኛ እናቶች ልጆቻቸውን ከስድስት ወር በኋላ ምግብ አስጀምረው ወደ ሥራቸው በሚመለሱበት ሁኔታ በዘመቻው ሙግቷን ቀጥላለች። ጎን ለጎንም አባቶች በልጆች ጉዳይ እናቶችን እንዲያግዙ በቂ የወሊድ ፈቃድ እንዲሰጣቸው የሚያስችለውን ዘመቻ ለመጀመር እንቅስቃሴም እያደረገች ትገኛለች።

እናት መደገፍ አለባት። በተለይ የኢኮኖሚው ሁኔታ ፈታኝ በሆነበት ጊዜ የአራት ወሩን ፈቃድ ማግኘቷ ተረጋግታ ቢያንስ እስከ ስድስት ወር ጡቷን በማጥባት ከእህል አገናኝታ ወደ ሥራ ለመመለስ ያስችላታል የምትለው ሮዝ በተለይ በአሁኑ ሰዓት ልጅ ወልዶ ለማሳደግ አጋዥ ቤተሰቦችንም ማጣት ፈተና እንደመሆኑ ለአባቶች በቂ የወሊድ ፈቃድ መሰጠቱ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብላ እንደምታምንም ትናገራለች። ፍቃዱ አባቶች እናት ከምግብ አገናኝታ ወደ ሥራዋ ስትመለስ ለሚያግዙበት ሂደት ይጠቅማል። ወገቧን አጎንብሳ ዳይፐር የምትቀይርበትን ድርሻ ከመውሰድ ጀምሮ ጉልበት ነክ ነገሮችን ፣ማጣጠቡንና ጡጦውን እንዲያግዙ ያስችላልም ትላለች።

እናት ጡት ለማጥባት በቂ ጊዜ ማግኘቷ ለሀገር የሚጠቅም ጥሩ ዜጋ ማፍራት ያስችላታል። ብዙ ሴቶችንም ሮዝ በዘመቻዋ እንዳሳካችው በጊዜ እንዲወልዱና በሥራና በእናትነት መካከል ያለውን ስጋት በመቅረፍ ይታደጋል። አባቶችም የሴቷን ጫና ለመቀነስ ፈቃዱን አግኝተው የድርሻቸውን ቢወጡ የተሻለ ቤተሰብ መመስረት ይቻላል። በመሆኑም ሮዝ የእናቶችን የወሊድ ፈቃድ ወደ ስድስት ወር ለማሳደግ እንዲሁም ለአባቶች ፈቃድ እንዲሰጥ የጀመረችው ትግል ለስኬት እንዲበቃ በመመኘት ጽሑፋችንን ቋጨን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ከስምንት አስርት ዓመታት በላይ ከዘለቀው አንጋፋው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጉዞና ትዝታዎች መካከል ጥቂቱን በወፍ በረር ቅኝት መራርጠን እንደተለመደው በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን አቅርበንላችኋል። ከመራረጥናቸው የጋዜጣው ቀደምት ዘገባዎች አብዛኞቹ ዛሬ ላይ ሆነን ስንመለከታቸው አስደናቂና ግርምትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ናቸው።

በዚህኛው ዘመን ከዩኒቨርሲቲ ተቋማት 238ሺህ ተማሪዎች መመረቃቸውን የሚገልጽ ዜና ብንሰማ ምናልባት ቁጥሩ ብዙም አነሰ እንላለን እንጂ አይገርመን ይሆናል። ስልሳ ዓመታትን መለስ ብለን የነበረውን ዘመን ስናስታውስ ግን 238 ሰዎች ማንበብና መጻፍ መቻላቸው 1950ዎቹ መጀመሪያ ትልቅ ዜና ሆኖ አዲስ ዘመን ጋዜጣ የፊት ገጽ ላይ ተቀምጦ እናገኘዋለን። “የኢትዮጵያን መሬት ቆርሰን እንዳንሰጥ ቃል ኪዳን ገብተናል” ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ለጋዜጠኞች ከሰጡት መግለጫ፣ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ነርስ ምን አለች፣ የአምቦ ውሃ ወደውጭ መላክ ስለመጀመር እና የኢትዮጵያን አውሮፕላን የመጥለፍ ሙከራ ስላደረጉት ወንበዴዎች የወጡ አስገራሚ ዜናዎችንም አካተን እንደሚከተለው ለትውስታ አቅርበናል።

### 238 ሰዎች በሦስት ወር ማንበብና መጻፍ ቻሉ

በአድአ ወረዳ ዕድገት ሚኒስቴር አማካይነት ለ3ወር የማንበብና የመጻፍ ችሎታ የሚያስገኝ ትምህርት ሲከታተሉ የቆዩ 238 ጎልማሶች ሚያዝያ 18 ቀን ባለፈው እሑድ ከሕዝባዊ ዕድገት ሚኒስቴር ከክቡር አቶ ጌታሁን ተሰማ እጅ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል።

ማክሰኞ ሚያዝያ 4 ቀን 1951 ዓ.ም

### የኢትዮጵያን መሬት ቆርሰን እንዳንሰጥ ቃል ኪዳን ገብተናል ግርማዊ ጃንሆይ ለጋዜጠኞች ጥያቄ የሰጡት መልስ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የካቲት 16 ቀን ትናንት የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞችን በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው በማነጋገር በኢትዮጵያና በሱማሌ መካከል ስላለው የወሰን ግጭት ሁኔታ መግለጫ ሰጥተዋል።

ጋዜጠኞቹ ስለጉዳዩ ከግርማዊነታቸው የተሰጠውን ማብራሪያ ካዳመጡ በኋላ፣ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን አቅርበው ነበር። ከጥያቄዎቹም መካከል አንደኛው የሱማሌ ሪፐብሊክ መንግሥት ታላቋ ሱማሌ በሚል መንፈስ የተከተለውን ዓላማ የማይለውጥ ቢሆን፣ በኢትዮጵያና በሱማሊያ መካከል ያለው ሁኔታ ምን ውጤት ያስከትላል የሚለው ነበር።

ለዚህ ጥያቄ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሰጡት መልስ “ኢትዮጵያ ከራሷ መሬት አንዲትም ስንዝር ብትሆን ቆርሳ አትሰጥም። የሱማሊያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከኢትዮጵያ ጋር በሰላም ተጎራብቶ የመኖር ፍላጎት ቢኖራቸውም የባህላዊ ቅርስ የንግድ፣ የግጦሽና የውሃ ግንኙነቶች ለማድረግ ይቻላል። ከዚህ የተለየ የምናደርገው ቸርነት ግን የለም። የኢትዮጵያን ዘውድ ስንደፋ በምንም አይነት ሁኔታ ከአገሪቱ መሬት ቆርሰን ለሌላ እንዳንሰጥ የሚያስገድደን ቃል ኪዳን በሕገ መንግሥታችን ላይ ሰፍሯል” የሚል ነው።

ማክሰኞ የካቲት 17 ቀን 1956

### የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ነርስ

“ነርስነት ለምልክት፣ ለደመወዝና ለሌላ ነገር የተሰጠ ስያሜ አይደለም። ሰው ሳያማርጡ በሽተኞችን በቅን መንፈስ ማገልገልና ታዛዥ መሆን ግን የነርስ ተቀዳሚ ሥራ ነው” አሉ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ነርስ ሲስተር ምሕረት ጳውሎስ።

የካቲት 26 1956 ዓ.ም

### የአምቦ ውሃ ውጭ አገር ሊላክ ነው

በቀን 116ሺህ ውሃ እያዘጋጀ የሚያቀርብ በአምቦ (ሐረር ሕይወት) እንዲቋቋም ስለታዘዘ በኢትዮጵያ ቴክኒክ ድርጅትና በኢጣሊያን ስታይም ኩባንያ ጋር የካቲት 27 ቀን ፩፱፻፶፯ ዓ.ም አንድነት ተፈርሚል።

ስምምነቱን የፈረሙት በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የመንግሥት ንብረት ስም አቶ ሀብተ አብ ባይሩ በረዳት ሚኒስትርነት ማዕረግ የቴክኒክ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ፣ በኢጣሊያ አጥኝነት ስራ አስፈጻሚ ኩባንያ በኩል ወኪሉ ሚስተር ማንካ ናቸው።

ሐሙስ የካቲት 28 ቀን 1957 ዓ.ም

### የኢትዮጵያን አሔሮፕላን ለማስገደድ የሞከሩት 2 ወንበዴዎች ተገደሉ

አዲስ አበባ፣ (ኢ-ዜ-አ) ከትናንት በስቲያ ማታ ከማድሪድ ወደ አቴን ሲበር ሳለ አቅጣጫውን እንዲለውጥ ለማስገደድ የሞከሩት ሁለት ወንበዴዎች በውስጡ በሚገኙ የአየር ኢንስፔክተሮች የተገደሉበት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነው ቦይንግ 707 ጀት አኤሮፕላን ትናንት ከእኩለ ቀን በፊት ከአቴን አዲስ አበባ ገባ።

በዚሁ ኤሮፕላን ከፍ ያለ የጀግንነት ሥራ የሠሩት የአየር መንገዱ ኢንስፔክተሮች፣ የኤሮፕላኑ ሠራተኞችንና የ2ቱን ወንበዴዎች አስከሬን ይዞ አዲስ አበባ ገብቷል።

ታህሣሥ 5 ቀን 1962 ዓ.ም

# ዓለም አቀፍ

## በአል-ሸባብ ታግተው የነበሩ 14 ኢራናውያን ከዓመታት በኋላ ተለቀቁ

በጋዜጣዉ ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በሶማሊያ በአል-ሸባብ ታጣቂዎች ታግተው የነበሩ 14 ኢራናውያን አሳ አስጋሪዎች ከዓመታት በኋላ ተለቅቀው ወደ አገራቸው መመለሳቸውን ቢቢሲ አስነበበ።

ታጋቾቹን ለማስለቀቅ ከመንግሥት ባለስልጣናት፣ ከጎሳ መሪዎች እና ከሶማሊያ የአገር ሽማግሌዎች ጋር ረጅም ድርድር ከተደረገ በኋላ መለቀቃቸውን የኢራን ዜና አገልግሎት ዘግቧል። ባለፈው ቅዳሜ ወደ አገራቸው የተጓዙት ታጋቾቹ በኢራን ደቡባዊ ክፍል ወደ ሚገኘው እና ቻባሃር ወደ ተባለው የትውልድ ስፍራቸውም አቅንተዋል።

ለሶማሊያ ቅርብ ከሆነው ዓለም አቀፍ የውሃ አካል ከታገቱት አሳ አስጋሪዎች መካከል እስከ 8 ዓመት በአል-ሸባብ ተይዘው የቆዩ እንዳሉም ተሰምቷል።

አሳ አስጋሪዎቹ ከመለቀቃቸው ከአንድ ወር ገደማ በፊት የሶማሊያ ፖሊስ በታጣቂዎች ተይዞ በነበረ ስፍራ ላይ 20 የውጪ አገራት ዜጎችን ማግኘቱን አስታውቆ ነበር።

ከእነዚህ ውስጥ 14 የኢራን ዜግነት ያላቸው ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ፓኪስታናውያን ናቸው ተብሏል። አል ሸባብ ድንበር ዘሎ በተለያዩ አካባቢዎች ከሚፈጽሙ ጥቃት ይሄኛው አንዱ እንደ ሆነም ተነግሯል፡፡



## ቻይና በታይዋን አቅራቢያ ግዙፍ ወታደራዊ ልምምድ አደረገች

በጋዜጣዉ ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ቻይና 71 የጦር አውሮፕላኖችን ያሳተፈ በታይዋን አቅራቢያ ግዙፍ ወታደራዊ ልምምድ ማድረጓ ተገለጸ፡፡

ሕዝባዊ ነጻ አውጪ ጦር በመባል የሚታወቀው የቻይና ጦር በአሜሪካ እና በራስዋ በምትመራው ደሴት እየተስተዋለ ያለውን ትንኮሳ ምላሽ ለመስጠት በሚል እሁድ እለት “ወታደራዊ ልምምድ” አድርጋለች፡፡

ከታይዋን የመከላከያ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ ወታደራዊ ልምምዱ እስካሁን ይደረጉ ከነበሩት እጅግ ትልቅ ነው ተብሏል፡፡

ሚኒስቴሩ በትዊተር ገጹ ላይ ባሰፈረው ጽሁፍ በልምምዱ 60 ተዋጊ ጄቶች የተሳተፉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቻይና ዘመናዊ አውሮፕላኖች እንደሆኑ የሚነገርላቸው ስድስት ሱ-30 የጦር አውሮፕላኖች ናቸው ብሏል፡፡

ከዚህም በላይ 47ቱ በደሴቲቱ የአየር መከላከያ መለያ ዞን ውስጥ ተሻግረው መግባታቸውን የአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ መረጃ ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ በልምምዱ ጥቅም ላይ ውለዋል ስለተባሉት አውሮፕላኖች ብዛት በቤጂንግ በኩል የተባለ ነገር የለም፡፡

ታይዋን የምትኖረው ዲሞክራሲያዊት ደሴት የግዛቷ አካል እንደሆነች በምትናገረው በቻይና የማያቋርጥ የመወረር ስጋት ውስጥ መሆኑ ይታወቃል።

በፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ የምትመራው ቤጂንግ አሁን ላይ በታይዋን የምታደርገው ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫናዋን ከፍ ማደረጓን ደግሞ የዚሁ ማሳያ ነው ተብሏል፡፡

ሩስያ በዩክሬን ላይ ወታደራዊ ዘመቻ መጀመሯ ደግሞ ቻይና በታይዋን ላይ ተመሳሳይ ነገር ልትሞክር ትችላለች የሚል ስጋት እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል፡፡

አሜሪካ ለታይዋን የምታደርገው ድጋፍ ደግሞ ሌላው ቻይናን የቀጠናው ውጥረት እያባበሰ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ይነሳል፡፡

በተለይም አሜሪካ ከቀናት በፊት ይፋ ያደረገችው ታይዋንን ለመርዳት የሚያስችል አዲስ የመከላከያ ህግ ደግሞ ቤጂንግን እጅጉን ያስቆጣ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡



ቤጂንግ የአሜሪካ ውሳኔ “በታይዋን የባህር ዳርቻ ሰላምና መረጋጋት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎች” የያዘ ነው ስትል አዲሱን ህግ ማውገዟም አይዘነጋም፡፡

# ስፖርት





# ኢትዮጵያ በብስክሌት ስፖርት ተስፋ ሰጪ ውጤት እያስመዘገበች ነው

**አስማማው ግዛው**

ኢትዮጵያን በኦሊምፒክ መድረክ በመወከል ቀዳሚ ከሆኑት ስፖርቶች መካከል አንዱ ብስክሌት መሆኑ ይታወቃል። እአአ ከ1956ቱ የሜልቦርን ኦሊምፒክ የሚነሳው የኢትዮጵያ የብስክሌት ስፖርት ተሳትፎ ከጥቂቶች በቀር እስከ 2020 የቶኪዮ ኦሊምፒክ ድረስ ኢትዮጵያን በመድረኩ መወከል ችላ። ስፖርቱ በኦሊምፒክ መድረክ በተሳትፎ ደረጃ የሚወሳ ታሪክ ይኑረው እንጂ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአህጉር አቀፍ እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየታዩ ነው።

በቀጣይ በፓሪስ የሚካሄደውን ኦሊምፒክ ጨምሮም በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤታማ ለመሆንም የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን እየተጋ እንደሚገኝ ጠቁሟል። የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌደሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍጹም ወልደአብ፤ የብስክሌት ስፖርት ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ በመወከል ከአትሌቲክሱ ቀጥሎ የሚጠቀስ ስፖርት እንደሆነ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ እያደረገ ሲሆን፤ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች በመመዝገብ ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል። በዚህ ዓመት በደቡብ አፍሪካ ራይድ ጆበርግ በተሰኘ ውድድር ላይ ኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳለያ ስታገኝ፤ በግብጽ በአዲስ መልክ በተጀመረው ናል ቱር ደግሞ የነሃስ ሜዳሊያ ማስመዝገብ መቻሉ ታውቋል፡፡

በፈረንጆቹ አዲስ ዓመት እንዲሁም እአአ በ2024 በፓሪስ በሚደረገው ኦሊምፒክ ላይም ውጤታማ ለመሆን የተለያዩ ስራዎች ከወዲሁ በመስራት ላይ ይገኛሉ። እአአ 2023 የአፍሪካ ቻምፒዮና እንዲሁም የዓለም ብስክሌት ቻምፒዮና የሚካሄዱ ሲሆን፤ ተወዳዳሪዎች ባላቸው ወቅታዊ ብቃት መሰረት ይበልጥ ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ወደ ዓለም አቀፍ ስልጠና ማዕከላት እንደሚላኩም ኃላፊው ይጠቁማሉ። ብስክሌት ጋላቢዎቹ የሚያገኙት ይህ ስልጠና መቀመጫውን በደቡብ አፍሪካ ባደረገው የስዊዘርላንድ የስልጠና ማዕከል ነው። በስልጠና ላይ የሚቆዩትም ለ2 ወር፣ ለ3ወር እንዲሁም ለ6 ወር ሲሆን፤ ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና እንደሚሰጣቸውም እንዲሁም የማጣሪያ ውድድሮችን ጭምር እንደሚያደርጉም አክለዋል፡፡

በተያዘው ዓመትም በዚህ የስልጠና ማዕከል ሶስት ብስክሌተኞች ስልጠናውን ወስደው ተመልሰዋል። ብስክሌተኞቹ በአውስትራልያ ኦሪንጎንግ በተካሄደ የዓለም ቻምፒዮና ተሳትፈውም ጥሩ የሚባል ውጤት እንዳስመዘገቡና ስፖርቱም በተሳትፎም ሆነ በውድደር ደረጃ በተሻለ መልኩ እንደሚገኝም ገልጸዋል። በተለያዩ የውጪ ክለቦች የኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች ያሉ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ በአሜሪካ፣ በፈረንሳይ እና በጣሊያን ክለቦች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህም ተወዳዳሪዎች በተለያዩ የአፍሪካና ዓለም አቀፍ ውድድሮች አገራቸውን በመወከል ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ ኪያ ጀማል፣ ሰላም አመሃ፣ ነጋሲ፣ ጽጋቡ ገብረማርያም ከብዙ በጥቂቱ ቢሆኑም ብዙ በውጪ ክለቦች ያሉ ተወዳዳሪዎች እንዳሉ ተነግሯል።

በዓለም አቀፍ ውድድሮች ከሚደረጉ ተሳትፎዎች በተጓዳኝም በመደበኛነት በአገር ውስጥ የተለያዩ ውድድሮች ይካሄዳሉ። ከነዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ቻምፒዮና በየዓመቱ በሰኔ ወር መጨረሻ ሲካሄድ፤ ለዓለም ዓቀፉ የብስክሌት ፌዴሬሽን ማሳወቅ ግዴታ ነው። በቻምፒዮናው አሸናፊ የሆነ ተወዳዳሪም በዓለም አቀፍ ክለብ ይኑረውም አይኑረውም የኢትዮጵያ አርማ ያረፈበት ጀርሲ (ማለያ) መልበስ የሚችለው የኢትዮጵያን ቻምፒዮና ተሳታፊ ሲሆን ብቻ ነው። ሌሎችም ውድድሮች ያሉ ሲሆን የክለብ ቻምፒዮና፣ የቱር ውድድሮች፣ የውጪ አገራት ተወዳዳሪዎች የሚካፈሉበት የአረንጓዴ ልማት ቱር፣ የክልሎች ውድድር፣ የታዳጊዎች ውድድር ናቸው። ይሁንና እነዚህ ውድድሮች አሁን እየተደረጉ አይደለም፤ ነገር ግን ለማስቀጠል በእቅድ ደረጃ መያዙ አብራርተዋል።

ብስክሌት የራሱ የሆነ የተሰጥኦ ስፍራ (ታለንት ኤሪያ) ስላለው በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ያለውን ተሰጥኦ አውጥቶ ለመጠቀም እየሰራ መሆኑንም ፌዴሬሽኑ ይገልጻል። እነዚህም ብስክሌት በብዛት የሚዘወተርባቸው እንደ ትግራይ፣ አዋሳና ድሬደዋ ናቸው። በአገሪቷ የመጣው





**በቶኪዮ-ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን የወከለችው ብስክሌተኛ ሰላም አመሃ፣**

የሰላም ተስፋ ለዚህም አስተወጽኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል። በዚህ ወቅት አስቸጋሪ የሆነው ውድድሮችን ከክልል ክልል ማድረግ ነው። ምክንያቱም ውድድር ሲደረግ መንገዶች ዝግ መሆን ይኖርበታል፤ ለዚህም ከምንም በላይ ሰላም ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ከዓለም 42ኛ ከአፍሪካ ደግሞ ደቡብ አፍሪካን እና ኤርትራን በመከተል 3ኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ፌዴሬሽኑ ባለፈው ዓመት ጠቅላላ ጉባዔውን ሲያደርግ ባቀረበው ሪፖርት ገልፆ ነበር፡፡


## ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

ኢስት አፍሪካ ኮሌጅ ከዚህ በታች በተገለጸው ክፍት የስራ መደብ ላይ ብቁ አመልካቾችን አወዳድሮ በቋሚነት መቅጠር ይፈልጋል። በመሆኑም ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች ከታች በተቀመጠው አድራሻ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ | የትምህርት ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ዓይነት | ብዛት | የሥራ ልምድ | የሥራ ቦታ | ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፕሬዚዳንት | ኤም ኤስሲ፣ ኤም ኤ፣ኤም.ቢ.ኤ እና ፒ.ኤች.ዲ | ቢዝነስ ማኔጅመንት ማርኬቲንግ ማኔጅመንት፣ኢኮኖሚክስ አካውንቲንግና ፋይናንስ ፣ ሎጀስቲክስና ሰፖላይ ቼን ማኔጅመንት ኮምፒዩተር ሳይንስ፣ የትምህርት አመራር እና ማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ ትምህርት መስክ የተመረቀ/የተመረቀች | 2 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ | አዳማ ካምፓስ | ለሥራው የእቅድ ፕሮፖዛል አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚችል/ የምትችል |
| 2 | ሱፐርቫይዘር | ኤም ኤስ.ሲ፣ ኤም.ኤ፣ኤም.ቢ.ኤ እና ፒ.ኤች.ዲ | ቢዝነስ ማኔጅመንት ማርኬቲንግ ማኔጅመንት፣ኢኮኖሚክስ አካውንቲንግና ፋይናንስ ፣ ሎጀስቲክስና ሰፖላይ ቼን ማኔጅመንት ኮምፒዩተር ሳይንስ፣ የትምህርት አመራር እና ማኔጅመንት ወይም በተዛማጅ ትምህርት መስክ የተመረቀ/የተመረቀች | 1 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ | አዳማ ካምፓስ ሆኖ የተለያዩ ካምፓሶችን በመሄድ መከታተል ይኖርበታል፡፡ | |
| | ሞጁል ኤዲተር ለሶሾሎጂ፣ለሩራል ዴቨሎፕመንት እና ለቢዝነስ | ኤም.ኤስሲ፣ ኤም.ኤ፣ኤም.ቢ.ኤ እና ፒ.ኤች.ዲ | በሶሾሎጂ ፣ሩራል ዴቨሎፕመንት፣ እና ቢዝነስ ማኔጅመንት በማስተርስ የተመረቀች | 1 | 2 ዓመት በላይ የሠራ/ች | አዳማ ካምፓስ | |

- ደመወዝ በኮሌጅ ስኬል መሠረት ሆኖ ተጨማሪ ጥቅማጥቅም ያካተተ
- ብቁ የሆነ አመልካቾች የትምህርትና የሥራ ማስረጃቸውን በመያዝ ዘወትር በሥራ ሰዓት ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 11፡30 ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ለተከታታይ 10 የሥራ ቀናት ኢስት አፍሪካ ኮሌጅ አዳማ ካምፓስ ከአዳማ ጀርመን ሆቴል ፊት ለፊት አዳማ ራስ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 49 በአካል በመቅረብ ማመልከት የምትችሉ ሲሆን
- በተጨማሪ በሚከተለው የኢ.ሜይል አድራሻ መላክ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡office@eauc.edu.et ወይም sallessarmolu@yahoo.com
- ማስታወሻ
- ለተጨማሪ መጃ የሚከተለውን ድህረ ገፃችንን ይጐብኙ www.eauc.educ.et telegram https://tme/eauatadama
- Facebook https//www.facebook com/eastafricacollegeadama

Office telephone 022-211-7474 or mobile 0916582735 or 0908202127

## ኢስት አፍሪካ ኮሌጅ